# መኽማኸ

## የሐረሪ ተረትና ምሳሌ

ከነ አማርኛው ትርጉሙ

አብዱራህማን መሐመድ ቆራም (ዶ/ር)

አዲስ አበባ መጋቢት 1984

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# መኽማኽ

## የሐረሪ ተረትና ምሳሌ

### ከነ አማርኛው ትርጉሙ

አብዱራህማን መሐመድ ቆራም (ዶ/ር)

አዲስ አበባ መጋቢት 1984

ካቲብዞ ሩኽሰ ብላይ ጣቢእ ሞሽ ኹቱሪንተ

ያለ ደራሲው ፈቃድ ማሳተም ክልክል ነው ፡፡

ጋሬ አባይ ጊስቲ ፋጡመ ሐጂ ቃኢዱው ቀጠብትሌ

ባለበቴ ወ/ሮ ፋጠማ ሐጂ ቃኢድን ለማስታወስ

NIGUSS

DIGITAL LIBRARY

# መ ቦ አ፤

ይ «መኽማኽ» ዛኔው ክታቡው ጌይ ኡሱኣች አርኩትዞም ራጋች መሕተፍዋ መቅነእሌ ዝኸሹሰአ ይትናፈኡቡዩ ዛላችን ተዩ ። ዝከተቦ ይነብራል ፣፤ ዝሐፈዞ ይትረሰኣል ባይቲው ቀጠብ ሞሸመ ዝወልዲ ወልድሌ መትዌረስ የትኺሻል ባይትቤ ፡ ራጋች አፍቤ ነሰእ ኔውመ ክታቡው ይቀሩ ዛላችሌ ከተብኔው ።

ጌይ ኡሱእ ሓላ መሐልዞዋ አር ስናንዞው መልመድሌ ይኸሹ ዛላች ኣሊማችዋ ቃሪኣችሌ ይ መኽማኻው አሕመረ ስናን ቱርጁምዞ በሕ ገበእ ንላነ ። ኩቱብዞው ቃሪኣችሌ ይነፊኩት ሊሒም ኡገቤ ሐጂስ ጌይ ሐርፊው መትኹተልቤ ቀረበ ።

ጌይ ስናን ኢትዮጵየቤ ዛሉ ሳሚ ስናናችሌ አሐድዝዩንተ ። ኢትዮጵየበ. ዛሉ አላይ ሳሚ ስናናች እሕመርኛ ፤ ትግርኛ ፤ ትግረ ፤ አርበጐብኛ ፤ ጋፋትኛዋ ፤ ጉራግኛን ተዩ ። ኢትዮጵየቤ ቃጪቤ ላሚ ስናን ይሴነንበዩ ዛሉ ባዳች በጂሕ ሐሉ ።

ሐረር ጌይቤ ይነብሩዛሉ ኡመታች ሩሕዝዩው «ጌይ ኡሱእ» ስናንዝዩውም «ጌይ ስናን» ይሉናር። ቱርጁምዞም ጌይቤ ይነብሩዛሉ ኡሱኣችዋ ስናዝዬ ባይቲንተ። ቃጪቤ ይዲጁ ዝናር ኡመታቹም ኻኑ ጊር ጌዩው ባድ ዝዩ ዛሹ ሰአ (ወልዳች ዝዩቤም ታ ጊር) ጌይ ኡሱእዩኹናሉ ። ዝነበሩቦ ቀቢለቤ ይጠረሑሜሉ ። ይም ዩኹናዛል ጌይ ኣደዋ ስናንዜም ቃም ዛሹ ሰኣንናር ።

አደሬ፣ይሎዛል፤ጨቅቲ ዚትነሰኤው «ሐደሪ» ይልዛል አረቢቤንተ ። «ሐደሪ» ባይቲ ጌይቤ ይነብርዛል ኡሱእ ባይቲንተ ። ይዞም ባዲየቤ ይነብሪዛል ዘልተ ኡሱእ ባይቲንተ ። ዘመን ጉድረቤዋ አረብ ስናኑው ፊዝቤ ዘለቤጃች «ሐደሪ» ይልዛሉ፡፡- አደሬ ኩፎኝ አናወጦ ። ሐረር ታሪኸቤ ጌይ ይሎዛሉው ዘትማለአቲ ሐረርጌይ ሙጢን ናርቲ ። ይሌ ባይቲንተ ጌይ ዛነሰአ፣፤ሐረር ጌይሌ ሙጢ ዝሰጤ ሱም ኩትኒትናፈእባዛነ ።

ሐረርጌይ (አውሮፓ ሒልቂቤ) ሳቲ በቅላች ዘመንቤ. ዚትዌጠንቲ ነትይታወቃል ። (፤) ጌይ ኢትዮጵየቤ ኢር ኪልቱጭ ደሌ ዛሉ ባዳችቤ ትጃረቤ ዝታወትቅ ቲን ናርቲ ። አሐድ በቅለ አመት በቀድበዞ ቡቲ እመቲዌጠን) ዜይለእ በሪቤ እላወሒንዲዋ ሸርቁል አውሰጥ ባዳች ኩፎኝ ዘባድ ፣፤ ከረቢ ፣ ዶኾን ሲን ዕቺ፷) ቡንዋ አላይ መሐዋቹም ኪሌኸቲ ፣ አዜ ይባዳቐበ. እራዝ ፣ ብረትቤ ዝደለገ መሐዋችዋ ሲያኽ ተዲጅናርቲ ። ኸሌው ወራሪው መትኻተርሴሌን ናር ።

በሪያች ባድ ኩፎኝ ይቡእዋ ዩጭዛል ኡሱእዋ መሐወ ይከትቡቦዋ ሚሪ የትኪፍሉቡዩ ዝናሩ አታያችን ናሩ ። በሪያች ሱማች ዝዩም አስመዲን በሪ ፣ አሱም በሪ ፡ አርጉበ በሪ፣ በድሮ በሪ፣ ሱቁጣጥ በሪን ቶተዩ ።

መትቦረድቤበም ይ መኽማኻው መሳሙቴ ሰአ ጊርጋረ ዛሹኛችሌ ፡-

1. ኣይ አመቱለ ዮሱፍ አብዲሌ
2. ኣይ ኣሸ አህመድ ሶፌ (አዩሌ)
3. ዶ/ር አብደለ አብዱናሲርሌ
4. አዲስ አበቤ ዛሉ ጀማአቹቺሌ አርኩት ሚስጋነ አሻኽኽ ።

ያመፔማኽ አሕመረስናን ተርጀመዞው ቀረኡመ ይንተ ዘነለ ፡ ኸጠእበ. ዝቄረሐኝ ኮበር (መምህር) ደርበው ኦዱኛሌ አር ኩት ሚስጋነ የቦርዲ እላኽ ። ይ ኩትዞ ጣቢእ መኪነቤ ዛሸሌኝ አቶ ኑርዬ ይማምሌም ሚስጋነ የቦርዲ ።

አ.መ. ቆራም

ኮተቤ ።

# መቅድም፡

በዚህ «መኸማኸ» በተባለው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ተረትና ምሳሌዎች ሐረሪዎች በተለይም ሽማግሌዎች የሚገለገሉባቸው ናቸው። «የተጻፈ ይወረሳል ፡ በቃል ያለ ግን ይረሳል» እንደሚባለው ይህንን ቅርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ አንዱ አመቺ መንገድ በጽሑፍ አማካይነት ስለሆነ ይኸው ለአንባቢያን ቀርቦአል ።

ይህ የሐረሪኛ ምሳሌና ተረት ከነ አማርኛ ትርጉሙ የቀረበበት ምክንያት ስለበሐረሰቡ ባህል ጥናት ለማድረግ ለሚሹ እና በአጠቃላይም በምሳሌያዊ አነጋገሩ ለመጠቀም ለሚፈልጉ አንባቢያን ሁሉ ይጠቅማል በማለት ነው ። ጽሑፉ ለአንባቢያን እንዲያመች ተብሎ ተዘጋጅቶ አዲሱን የሐረሪኛ የፊደል ተራ በመከተል ቀርቦአል ።

የሐረሪኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ ካሉት የሴም ቋንቋዋች አንዱ ነው ። ሌሎች በኢትዮጵያ ያሉ የሴም ቋንቋዎች አማርኛ ፥ ግዕዝ ፡ ትግርኛ ፤ ትግረ ፤ አርጎብኛ ፡ ጋፋትና ጉራግኛ ናቸው ። ከኢትዮጵያ ውጭ የሴም ቋንቋዎች የሚነገሩባቸው ሀገሮች በርካታ ናቸው ።

ሐረሪዎች ራሳቸውን «ጌይ ኡሱእ» ቋንቋቸውን ደግሞ «ጌይ ስናን» ብለው ይጠራሉ ። ትርጉማቸውም «የከተማ ሰው እና የከተማ ቋንቋ ማለት ነው። ወደ ከተማው መጠ የሆኑ ሁሉ የጐሳ መጠሪያቸውን ትተው የከተማዋን ባህልና ቋንቋ እንደወሰዱ (ምናልባትም ልጆቻቸው) ኣደሬዎች ይሆናሉ ።

አደሬ የሚለው ቃል ከአረብኛ «ሐደሪ» ከሚለው ቃል የተወሰደ ነው። «ሐረሪ» የሚለው የከተማ ሰው ማለት ሲሆን ኑርሱም ገጠሬ ከሚለጡ- ለመለየት የሚሰየም ነው ። ምናልባትም ኦረብኛን በቅጡ ያላጤኑ ሰዎች «ሐደሪ» የሚለውን «አደሬ» ወደ ሚለው ቀይረው ታል ። 6ታሪክ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሐረር ክፍለ ሀገር በከተማነት ትታወቅ የነበረች የሐረር ከተማ ብቻ እንደነበረችና ይህም በኣደርኛ «ጌይ» ሲባል ከተማ የሚለውን ለሐረር ከተማ ብቻ እንዲሰጣት ያደረገው ዋናው ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን ።

የሐረር ከተማ እ ኤአ በ7ኛው ክፍለ ዘመን እንደተቆረቆረች ይታወቃል ። ሐረር በምሥራቅ ኢትዮጵያ የታወቀች የንግድ መናኸሪያ ነበረች ። የዛሬ መቶ አመት በፊት (ጂቡቲ ከመመስረቷ በፊት) እንኳ በዜይላእ ወደብ ወደ ሕንድና የመካከለኛ ምስራቅ ሀገሮች ዝባድ ፤ ከርቤ ፤ የዝሆን ጥርስ ፤ ቡና ወዘተ በመላክ እና ጨርቃጨርቅ ፡ የብረት ውጤቶችንና ጌጣጌጥ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ከፍ ያለ ንግድ ታካሄድ ነበር ።

የሐረር ከተማን ከሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ለየት የሚያደርጋት የጥንት ክፍለ ከተማዋ ዙሪያ በግንብ መታጠርዋ ነው ። ማታማታ ተዘግተው ጧት ጧት የሚከፈቱ አምስት በሮች ነበርዋት ። ግንቡም የተሰራው በአሚር ኑር ዘመን ሲሆን በከተማዋ ነዋሪዎች ላይ ይቃጣባቸው የነበረውን የተደጋገመ ወረራ ለመከላከል ነበር

በሮቹም ወደ ከተማዋ የሚገቡትንና ወደ ውጭ የሚወጡትን የንግድ እቃዎችና የውጭ ሀገር ሰዎች መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ እንዲሁም ቀረጥ መቅረጫ ቦታዎች ነበሩ ። በጠቅላላው የበሮቹ ስሞች የሚከተሉት ናቸው ። እነርሱም አስመአ ዲን በሪ ፣ አሱም በሪ አርጐብ በሪ ፣ በድሮ በሪ እና ፤ ሱቁጣጥ በሪ ናቸው ።

በመጨረሻም ይህን የአደርኛ ተረትና ምሳሌ ስሰበስብ ከፍ ያለ እገዛ ላደረጉልኝ ፡---

1. ለእመት አመቱላ ዩሱፍ አብዲ
2. ለእመት ኣሻ አህመድ ሶፊ አናቴ)
3. ለዶ/ር አብደለ አብዱናሲር
4. ለአዲስ አበባ «ጀማአዎቼ» #ደኞቼ)

ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። በተጨማሪም የዚህን «መኸማኸህ» የአማርኛ ትርጉም አንበው ይህ ነው ከማይባል ስህተት እንድጠበቅ የረዱኝን መምህር ደርበው አዱኛን በጣም አመሰግናለሁ ። እንዲሁም ጽሑፉን በታይፕ ለመቱት ለአቶ ኑርዬ ይማም ምስጋና አቀርባለሁ ።

አ. መ. ቆራም

ኮተቤ ።

ጌይ ስናን መፔማኸዞ ዚትከተበበው ሐርፊያች
የአደርኛ ተረትና ምሳሌው የተጻፈበት ፊደላት ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሐ | ቀ | አ | ደ |
| ለ | በ | ከ | ጀ |
| መ | ተ | ኸ | ገ |
| ረ | ቸ | ወ | ጠ |
| ሰ | ነ | ዘ | ጬ |
| ሸ | ኘ | የ | ፈ |

| ሐረሪ | አማርኛ |
| --- | --- |
| 1. ሐለኝ ባይቲ እዳወ ይሰብራል። | 1. አለኝ ማለት ጠላትን ያሳፍራል። |
| 2. ሔምድ ኢሕዞ ቱምቦኹ። | 2. የአመድ ወንድሙ ትምባሆ። |
| 3. ሐማቺ አይቅበር ዝቅበሬውው ያጫል። | 3. አማች አይቅበር የቀበረውን ያውጣል። |
| 4. ሐሚስቲ አጣብኙቤ ደረርዝኻነሌ ደዋም ኤለ። | 4. በአምስት ጣት (በምግብ) ለተጐዳ መድኃኒት የለውም። |
| 5. ሐይበይሌ መረኸሰችኺ የቅለቅሰኸሌ። | 5. እንኳን መረቅ ጠጣህ ሊያሸርህ። |
| 6. ሐም ብላይ የኸ ዘዩቅ። | 6. አምጣን እንጂ እንካን አያውቅም። |
| 7. ሐረሬ ኸጊር ከሰ ሐራረ መረሬኸጊር ደው ምራር። | 7. ከተናደድህ የሞራ ጥብስ ከመረረህ የፍየል አሞት (መናደድ የለብህም የንዴት ትርፉ ራስን መጉዳት ነውና) |
| 8. ሐርአት ኢጊር ዛለ ጋሚላውም አሐድ ጊር የዝላሕጠሐል። | 8. አራት እግር ያለውን ግመል እንኳ አንዴ ያዳልጠዋል። |
| 9. ሐርሺአተዋቅ ጌይ አተዋቅቱኹኑሜት። | 9. ቆቅ ዶሮ አትሆንም። |
| 10.ሐርሺ ዛላው ሐርየ ሰደዴው። | 10.ባለ እርሻውን አሳማ አባረረው። |
| 11.ሐሳዱው አብሱመዘ ገደሌው። | 11.ቁልቋልን የልጁ ልጅ ገደለው።+BA11:B12 |
| 12.ሐያእ ዘሌለ ኢንጭገር ሼለደ። | 12.ሕፍረተቢስ ቅንድቡን ይላጫል (ሐረሪዎች በባህላቸው ቅንድብ መላጨት ከብልትና አሠራር ጋር ስለሚያመሳስሉት ነው። |
| 13.ሐይ ዝቀበጠ አብስቤ እመል አሸ። | 13.ወተት ያጣ አሬራ ይጠጣ። |
| 14.ሐይለኘ ኢንዞ ኢቢእ። | 14.የኃይለኛ ዓይኑ እንባ (ሲከለከል) ። |
| 15.ሐደይ ዞለአ ሲንዞቤ እሰጠ። | 15.ያልሰረቀ (በቀላሉ) አልከበረ። +A11:B12+A1:C682 |
| 16.ሐጂሰ መኸረ ሐጂስ አፈር ያጫል። | 16.አዲስ መቆፈሪያ አፈር ያወጣል (መጤ ሰው በአዲስ ጉልበቱ ብዙ ሲሠራ ሲታይ ወይም ሊታይ ሲል የሚነገር |
| 17.ሐጪው ከርሲ መረጤው። | 17.ጀርባን ሆድ ገፈፈው (ሆዳም ሰው አይተርፈውም) ። |
| 18.ሐፍ ዘላሸ ሐፍ ይሉሜል። | 18.ያልሰረቀ (በቀላሉ) አልከበረ። |
| 19.ሐሉፍ ይለኸ ቄሲ ኣውኸ ጋር ጋፊ የግዘአኸ። | 19.እስኪያልፍህ ያባትህ ሎሌ ይግዛህ (እስኪያልፍ ያለፋል። ማንኛውንም ነገር መቻሉ ይበጃል) ። |
| 20.ሐፍ ዛዩቦ ነቱ እሩዝ መውጠኢንተ። | 20.የዳኑበት በሽታ ከመሞሸር ይቆጠር። |
| 21.ሑል ዝቀበጡሎሌ ሑለ ቀደዱሎ። | 21.ጎመን ላጡሰት ሓር ቀደዱለት (በቁመናው አልረዱት ከሞት ወዲያ አዘኑለት) ። |
| 22.ሑሩብ ባዮጊር ጩር ይልዛል። | 22.ፉት ሲሉት የሚፈስ (ሲያቀርቡት የሚርቅ) ። |
| 23.ሑባቡው ገደሎጊር ትነበርትዞ ኡሱው ጠለኦ ጊር ተንዲነትዞ። | 23.እባብን ሲገድሉ ከነበትሩ ሰውን ከጠሉ ከነገንዘቡ። |
| 24.ሑባብ ወልዲ ሒፊኝ። | 24.የእባብ ልጅ እፉኝት። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 25.ሑባቤ ሲከ ሒፊኝዼ ሑር። | 25.ከእባብ አምልጦ ወደ እፉኝት ሩጦ። |
| 26.ሕራር ፊገ አውዞው ገደለ። | 26.የቁጣ ሩጫ ባለቤቱን ገደለ። |
| 27.ሒራር ዝቀደሜው ሴነ ቴሐረቤው። | 27.ቁጣ የቀደመው ጸጸት ተረፈው። |
| 28.ሒርግቤ ዛሾ ፊስ ይጪቁሜል። | 28.በምክር የፈሱት አይገማም። |
| 29.ሒስትዋ ስናን ጥቀሾዘ ዮቃል። | 29.ነገርና ምቀኝነት ይበቃል በጥቂት። |
| 30.ሓላ አመል ይጊዙሜል። | 30.ጠባይና ልምድ አይለቅም። |
| 31.ሑለተኘ አደዞ በጂሕ። | 31.የሰነፍ መሣሪያው ብዙ። |
| 32.ሑለትቤ በጂሕ ይጠፋል። | 32.በስንፍና ብዙ ይጠፋል (ሰው ከሠራ ብዙ ነገር ያገኛል። በመስነፉ ደግሞ የሚወር ሰው ድህነትን ብቻ ነው) ። |
| 33.ሐጂ ቡቺኤው ዝመሐጠ ጊዘ ኣኑው ይመሕጠኝሌ ቁረቤ ሐል። | 33.ዛሬ ውሻዬን የመታ ነገ እኔንም ሊመታ ተቃርቦአል። |
| 34.ሖጂ ዘላረዶው ጊሽ እየግኞ። | 34.ዛሬ ያላስቀመጡትን ነገ አያገኙትም። |
| 35.ሉኽ ኤቀዱው ይፈሩሜል። | 35.መልዕክተኛ ሹም አይፈራም። |
| 36.ሊጂ ዝቀበጠ ቀሐት የትፊቅራል። | 36.ወንድ ልጅ የሌለው ሴት ልጅ ያጫውታል። (በባህሉ ወንድ ልጅ ስለሚወደድ ነው።) |
| 37.ሳም ዝሞቄ አታይቤ ቲኘኣት። | 37.ላም እሞቃት ቦታ ትተኛለች። |
| 38.መሐወ ኣውዞኩት። | 38.ዕቃ እንደ ባለቤቱ። |
| 39.መሕ ይሎዛል ይነኽስዛል። | 39.እየሳሙት የሚነክስ። |
| 40.መሐምጥ ዘዩቅ ወልዲ ቁይሌ በከ። | 40.የማይቀጡት ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል። |
| 41.መሞተ ዘበልቲ ራጊቱው ወልዲ አጤወሬ። | 41.አልሞት ያለችውን አሮጊት ልጅ አሸከሙአት። |
| 42.መረኽ መኸሸ በሰርሌንተ። | 42.መረቅ ፍለጋ ለሥጋ። |
| 43.መሰጠ ዘዩቅ ዜገ ሳቲ ጊርዴረ ቦአ። | 43.መስጠት የማያውቅ ድሀ ስባቴ ጓዳ ገብቶ ይወጣል። |
| 44.መሸሕ እሳል በሰር የሖንቊሜል። | 44.ቢላዋ እያለ ሥጋ አያንቅም። |
| 45.መቀጡቤ ዝገደረ ኣጥ። | 45.ከማሰሮ የተለቀ አጥንት። |
| 46.መቀጡቤ ዘሌሉው አምስቲ ይስጡሜል። | 46.በማሰሮ ውስጥ የሌለውን መጭለፊያ አይሰጥም። |
| 47.መቆሸትመ ሰእይቤ ትሊጥዛት ፉሩው መቆሸት ዞሌቀሰጠ። | 47.ቡሀቃ ላይ የምትሄደውን አይጥ ለቡሀቃው ብለው ተዋት። |
| 48.መቴርመር ዘዩቅ ሜመር ዩቁሜል። | 48.መታዘዝን የማያውቅ ማዘዝን አያውቅ። |
| 49.መትፋለስ ዝኸሸ የሞት መሰደብ ዝኸሸ ኢንዶች የፍትሕ። | 49.ለመሞገስ ያሻ ይሙት ለመሰደብ ያሻ ሚስቱን ይፍታ። |
| 50.መንሰአቤ አሐዱም ኤልባም መትሔደርቤ ብላይ። | 50.ማስተዳደሩ እንጂ ሚስት ማግባቱ አይቸግርም። |
| 51.መንበርትቤ ተሐይሌ ዛል ዝሞታተ። | 51.ከመኖር በታች ያለ የሞተ ብቻ። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 52.መገንተ ዘየሎ አይመሐጠነ። | 52.የማይማለዱት አይምታን። |
| 53.መጦቀስ ነቱ ቅባጭዞ | 53.መለመን በሽታ ማጣቱ ሞት። |
| 54.መጤነ ዝኸሸቲ ወጨረሙ ሳፈር ጋር ተሕሪ። | 54.እንድትጫን የፈለገች አህያ መንገደኛ ቤት ትሔዳለች። |
| 55.ሙራድ ነሲቢንተ ጪልመቤ ዝገኞ ኡኒንተ። | 55.ጋብቻ በዕድል በጨለማም እንደ ተጣለ ድንጋይ ነው። |
| 56.ሙርጠ ዘላሹሎ ሹርቤ ተረእ። | 56.አልተጋበዘ ገንፎውን ላይበላ ይምላል። |
| 57.ሙትበለቼዞ ሺኢሽቲያም። | 57.የሙት ሠርጉ ሦስት ዕለት። |
| 58.ሙት ዳኢሙም ሐጂስ። | 58.ሞት ሁሌም አዲስ። |
| 59.ሙት ይትለመዱሜል። | 59.ሞት አይለምዱትም። |
| 60.ሙት ይፈሮመ ጋዝ ይቀሮሜል። | 60.ሞት ፈርቶ ከጦርነት አይውሉም። |
| 61.ሙትሴ መገኑም ኤለ ዝሞተሴ መርገገቡም ኤለ። | 61.ሞት አይማጠኑት የሞተ አይመለስም። |
| 62.ሙትዋ መኚት መሳንተ። | 62.ዕንቅልፍና መኝታ መሳ ለመሳ። |
| 63.ሙዘይሲ ወራብ አየግኘነ። | 63.የማይጮህ ጅብ አያግኘን። |
| 64.ሙትዋ ሙራድ መሳንተ። | 64.ሞትና ጋብቻ መሳ ለመሳ። |
| 65.ሙትዞ የትረኸብ መብከ የሙሱሜል። | 65.መሞቱ ከተገኘ ማልቀስ አያዳግትም (ችግርን እንደ አመጣጡ እንቋቋመዋለን) ። |
| 66.ሙጢ ማጥ እኺረ ዋይ። | 66.ብቻውን የበላ ብቻውን ያለቅሳል። |
| 67.ሙጐት ፊሪ ወልዲም አለሴቀ። | 67.ብድር የፈራ ልጅ አላሳደገ። |
| 68.ሙጐት ይራጊተል ብላይ ይሙቱሜል። | 68.ብርድ ያረጃል እንጂ አይሞትም። |
| 69.ሙጢዞ ዞሊእ ሙጢዞ ይሙታል። | 69.ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል። |
| 70.ሚስኪነት ዝኸሸ ቀሐት የቦርዲ፤ ባውነት ዝኸሸ ቀሰም የሴብሪ። | 70.መደህየት ያሻ ሴት ልጁን ይዳር መከበር ያሻ ለልጁ የትምህርት ምርቃት ያዘጋጅ (እርዳታ ስለሚሰጠው) ። |
| 71.ሚስኪን ነኪኦትዞ እጤዞቤ ይባራል። | 71.የድሀ መበደሉ ከራስ አይርቅም። |
| 72.ሚስኪን ነኪኦትዞ እጤዞቤ ይባራል። | 72.ምን ይለሰልሳል ቢሉ ጉበት ምን ይጠጥራል ቢሉ ሆድ። |
| 73.ሚይ መላቅ ቀሐቱው ሚይ ገደዲ። | 73.የውሀ አከፋፋይን ልጅ ውሀ እጦት አጠቃት። (የኩሬን ውሀ በመስኖ ለሚጠቀሙ ገበሬዎች ሐላፊው ስለሚያከፋፍል ነው) ። |
| 74.ሚይቤዲጀ ሚይቤ ሴጠ። | 74.በውሀ መጣ በውሀ ሄደ። (ሳይቸገሩበት ለተገኘ |
| 75.ሚሕረ ዝቀበጠ ከፍቾር ሲን ወቀጠ። | 75.ሥራ የፈታ የአንበጣ ጥርስ ነቀሰ (በሆነ ባልሆነ ነገር ጊዜውን ለማያልፍ ሰው የሚነገር ነው።) |
| 76.ሚን ቀደመ አደብ ሚን ቴሐረ ነሰብ። | 76.ምን ቀደመ ቢሉ ስነ ምግባር ምን ተከተለ ቢሉ መወለድ (የሰው መከበሪያው ምግባሩ) ። |
| 77.ሚን የሉኘ ዘላያው ወራበ በለኤው። | 77.ይሉኝታ የማያውቅን ሰው ጅብ በላው። |
| 78.ማልቱ ሑባብ ዝሪእ ምሼት ፈቲትቤ ባረገ። | 78.ቀን እባብ ያየ ማታ በገመድ በረየ። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
| --- | --- |
| 79.ማን አሌቄው ብላይ ማን ወለዴው ይሎሜል፡፡ | 79.ማን አሳደገው እንጂ ማን ወለደው አይሉም፡፡ |
| 80.ምሬኘዋ ቁመኘ ይትፈራሉ | 80.ጣውንትና ቡዳ ይፈራሉ፡፡ |
| 81.ምሼት ይሊጡቦው ማልቱ | 81.ማታ የሚሄድበትን ቀን ያበጃጁ፡፡ |
| 82.ሞለሕቤ ሚይ ሜሰብ፡፡ | 82.በመሣሪያ ድንጋይ ላይ ውሃ ማፍሰስ፡፡ |
| 83.ረሐቤኘሌ ጢሪ መረጪ አይንጮ ጠረሬኘሌ በድሮ ሰሪ ማገቱው አይስቾ፡፡ | 83.ለረሀብ ጥሬ አንጀት አይበሉ፤ ለውሀ ጥም የበድሮ በርን የቦይ ውሀ አይጠጡም፡፡ |
| 84.ረሕመት ዘሌልባሕ አይዳብለነ፡፡ | 84.ርህራሄ ከሌለው ጋር አይግጠመን፡፡ |
| 85.ረቀ ሐርሺዞቤ ኣቂል ዘረአቤው፡፡ | 85.የሞኝን እርሻ ብልጥ ዘራው፡፡ |
| 86.ቀረሌ ሐይ ጢሪዞ ዱሰ ቀመነዞ፡፡ | 86.ለሞኝ ወተት ጥሬው ማር ኮምዛዛው፡፡ |
| 87.ረቀሌ ሙሉእ ብላይ ቁቡሉም ኤለ፡፡ | 87.ለሞኝ ሙሉ እንጂ ጎደሎ የለውም (ሲናገር አያመዛዝንም) ፡፡ |
| 88.ረቀ ስናንዞሌ ኢንፊጥዞኩት እታይ ይሒጅ ላሜል፡፡ | 88.ሞኝ እንደ ንፍጡ ሰንግግሩም ቦታ አይመርጥለትም፡፡ |
| 89.ረቀ ሺኢሽቲ ጊር ኾሳር፡፡ | 89.ሞኝ ሦስቱ ይክሰር፡፡ |
| 90.ረቀበሕ ይትፌቀሮቤ ኣቂል በሕ በርቲ በርቲ ዩሾ፡፡ | 90.ከሞኝ ጋር ከሚጫወቱ ከብልህ ጋር በብትር ይማቱ፡፡ |
| 91.ረቀ ባዩሎ ጊር ዛዩቦ ይመስለሐል፡፡ | 91.ሞኝ ቢሉለት ያሉበት ይመስለዋል፡፡ |
| 92.ረቀ ቱምባኾኩት ስሚቤዛል ዳነሌ ይረጥሳል፡፡ | 92.ሞኝ እንደ ትምባሆ በሰማይ ላለ ደመና ይረጥባል፡፡ |
| 93.ረቀ ወደዶ ጊር ዘለዶ ይመሰስሐል፡፡ | 93.ሞኝ ከወደዱት የወለዱት ይመስለዋል፡፡ |
| 94.ረቀዋ ረቁ ይመራል፡፡ | 94.ሞኝና መተሬ ይመራል፡፡ (የሞኝ ቃል እንደ መተሬ ይመራል) ፡፡ |
| 95.ረቅይሲሕቅመ የሲሕቃል፡፡ | 95.ሞኝ ስቆ ያስቃል፡፡ |
| 96.ረቃው ቀብሪ እቱሮ ጋር ዩቡእበሐለ፡፡ | 96.ለሞኝ መቃብር አያሳዩም ቤት መስሎት ይገባበታልና፡፡ |
| 97.ረቃው ቲርትረት ፉቱሕ ቁዱጽ አልመሰሌውም፡፡ | 97.ሞኝን የግርጌ ልብስ መተርተር መቀደድ አይመስለውም፡፡ |
| 98.ረቃው ዝሐተፎ ያም ቱኻኑው ዘረገፎ ያም፡፡ | 98.ሞኝ የመከሩት ለት ትኋን ያረገፉት ለት፡፡ |
| 99.ረቃው ዞደለ ቀብሪቤ መኘት ቀበጠ፡፡ | 99.ሞኝን የወለደ በመቃብር እንቅልፍ አጣ፡፡ |
| 100. ሩሕሌ ዛዮ ሹር ይቀጥኑሜል ኡሱእሌ ዛዮ ይወድሉሜ፡፡ | 100. ለራስ ያሉት ገንፎ አይቀጥን ለሌላ ያሉት ግን አይወፍርም፡፡ |
| 101. ሩሕሩሕዜው አትሪእ ቡቺ ጫየዘው እትሪእ፡፡ | 101. ነፍስ ራሷን ውሻ ጥላዋን አታይ፡፡ |
| 102. ሩሔቅቤ ዛል አሕሊቤ ቁረቤ ዛል አለገ ይማጅ፡፡ | 102. ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጐረቤት፡፡ |
| 103. ሩሕ አፈርዜሌ ትበካት፡፡ | 103. ነፍስ ለ (ትውልድ) አፈርዋ ታለቅስ፡፡ |
| 104. ሩሑቅቤ ዛል አረ ኡፍ ይሰዱሜል፡፡ | 104. ሩቅ ያለ ማማ ወፍ አያባርርም፡፡ |
| 105. ሪኡኝ ሪኡኝ ይልዛል ሼምቁኘሌ ቁረቤ ሐል፡፡ | 105. አለሁ አለሁ የሚያበዛ ደብቁኝ ደብቁኝ ይላል፡፡ |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 106. ራገ ዘሌልበ ባድ ይገራል። | 106. ሽማግሌ የሌለበት ሀገር ባዶ ይቀር። |
| 107. ራግነቱም አለራጌኝ አታ በርን እራጌኝ ይብላ። | 107. ያስረጀኝ በዕድሜ መቆየቱ ሳይሆን የቤት ውስጥ ጭቅጭቁ ነው እንጂ። |
| 108. ራግኺ ጊር ቆርኻሌ ቢከ ዘልባድ ሓርኺ ጊር ሊማዋ ነሰብኻሌ ቢክ። | 108. ካረጀህ ለመልከህ ከተሰደድህ ለትውልድ አልቅስ (ስለማትታወቅ) ። |
| 109. ራጐው ዝሐደጐ ወሬጐው። | 109. ሽማግሌ የተተወ ጌጥ። |
| 110. ራጡው ዝቃነነበው ዩቀሐል። | 110. ረመጥን ያሚያውቃት ይረገጣት። |
| 111. ሮጂ ቶየውዞ ዩሩጁሜል። | 111. ሌባ ጐረቤቱን አይሰርቅም። |
| 112. ሰሐቅ ቢዝሐ አባር። | 112. የሳቅ ብዛት ረሃብ (ያስከትላል) ። |
| 113. ሰሚቤ ዝዲጀ ዝናቡው ደቺ ይትቄበለሐል። | 113. ከሰማይ የሚወርደውን ዝናብ መሬት ይቀበለዋል። |
| 114. ሰምቤ ሰላመት ዩጬ። | 114. በዝምታ ሰላም ያገኙአል። |
| 115. ስምቲ ዝቄሕ ኢንተ መሴነን ሜት ኢንተ መትጋጋደል ነሐስ ኢንተ። | 115. ዝምታ ወርቅ መናገር መዳብ፥ ጠላት ነሐስ። |
| 116. ሰም ዛየ አፍቤ ዚምቢ ይቡኡሜል። | 116. ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም። |
| 117. ሰም ዛየሌ ኣይዞም ሕራት እልሰጥተ። | 117. ዝም ላለ ልጅ አናቱም ራት አልሰጠችው። |
| 118. ሰሪ ሓሮ ጊር ሚስሊ ኻድ ኢንጪ ዩቀጬሐል። | 118. ጋራ ቢወጡ ራስን መሰል እንጨት ይቆርጡ። |
| 119. ሰሪቤ ሳር መጋለቤ ሰበር። | 119. በተራራ ሳር በገበያ ስጋ (ሞልቷል) ። |
| 120. ሰበብ ናሬኝ ጥጃ ኼጀኝ። | 120. እንኳን ሰበብ ኖሮኝ እንዲያውም ጥጃ ረግጦኝ። |
| 121. ሰናቢ ኡሲራ ሐሚስቴሌይ ቀጥኑሜል። | 121. ሰናፍጭ ለአሥራ አምስት ቀን አይቀጥንም። (ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ እንደማለት ነው) ። |
| 122. ሱቡር ለእይቤ ጠር። | 122. ከሰባራ ላይ ሰንጣራ። |
| 123. ከሰባራ ላይ ሰንጣራ። | 123. ሰባራ በሰንጣራ አለው ቅሬታ። |
| 124. ሱዱብ ይሰድባል ፉሉስ ይፉልሳል። | 124. የሚሰደብ ሌላውን ይሰድባል የሚሞገስ ያሞግሳል። |
| 125. ሱጊየ ይኹኖመ ደም ይፈሮሜል። | 125. አራጅ ሆኖ ደም አይፈሩም። |
| 126. ሱጢ ዛልበ ዳግ ቾፍ ይሱሜል። | 126. ኮሶ ያለበት አይዘልም ከዳገት። |
| 127. ሲበ ሰም ይልመ መስቲከከሕ ይላል። | 127. ማሰሮ ዝም ሲል መጭለፊያው ይጮሃል (አዋቂ ዝም ብሎ ያላዋቂ ሲናገር የሚተረት) ። |
| 128. ሲበ ኡስጡ መኸቱት። | 128. የጋን ውስጥ መብራት። |
| 129. ሲኑም ሲኔዜ በሕ ቲሲሕቃት። | 129. ጥርስ ከእኩያዋ ጋር ትሳቅ። |
| 130. ሲን ሱበር ስናን ሱበር። | 130. ጥርስ ሸራፋ ነገር ኮልታፋ። |
| 131. ሲን ዘሌለ ዲዲሕቤ ይሲሕቃል። | 131. ጥርስ የሌለው በድዱ ይስቃል። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 132. ሲንዜው ዝሪኤ ቀሐቱው ሳተልቃምዜው ሪኤ። | 132. ጥርስዋን ያዩዋትን ልጅ ሁለመናዋን እዩዋት። |
| 133. ሲንዞው ብላይ ከርሲዞው ዘይርአ። | 133. ጥርሱን እንጂ ሆዱን የማያዩት። |
| 134. ሳስ ሲንቤ ዞጨ ሳሰ ጋር ቦአ። | 134. ከሰላሳ ጥርስ (ከአፍ) የወጣ ለስላሳ ቤት ተዳረሰ (ነገር አንዴ ከአፍ ከወጣ ሁሉም ስለሚሰማው መጥፎ ከመናገር መቆጠብ ይሻላል) ። |
| 135. ሳቅ ዘሌለ ሳሒቡም ኤለ። | 135. ገንዘብ የሌለው ጓደኛ የለው። |
| 136. ሳቅ ዘሌሰ መጋለ ይቡኡሜል። | 136. ገንዘብ ያጣ፤ ገበያም አይወጣ። |
| 137. ሳቲ አያም አንጦር ዛየ ዘቲ አመት ጦር። | 137. ሰባት ቀናልችል ያለ ሰባት ዓመት ተሸከመ። |
| 138. ስናን ስናን ዩልዳል። | 138. ነገር ነገርን ይወልዳል። |
| 139. የስናን ቁቡሉው ሰሐቅቤ ይመሎሖል። | 139. የነገር ጐደሎን በሳቅ ይሞሏል። |
| 140. ስናናም ኡገቤ ጋር ይቺኸላል። | 140. ነገረኛ መንገድ ላይ ቤት ይሠራል። |
| 141. ስናን ኦኾሌዞ ሐየንተ። | 141. ስናን ኦኾሌዞ ሐየንተ። |
| 142. ሰናናምሌ ኡገ ሕደጉሎ፥ ከርሳምሌ ገበተ ሐደጉሎ። | 142. ስነገረኛ መንገድ ለሆዳም ገበታ ይተዋል። |
| 143. ስናን ይኸሾው አባትኻቤ ጋር ከረ ሲጥ። | 143. ነገር የምትሻ ሆይ በግቢህ ቤት አከራይ። |
| 144. ሹሩፍ ይሸርፋል፥ ሱዱብ ይሰድባል። | 144. ሸራፋ ይሸርፋል የሚሰደብ ይሰደባል። |
| 145. ሹሩው መሐሌ ይሒኮሖል። | 145. ገንፎን ለነውር ያኽኩአል። |
| 146. ገንፎን ለነውር ያኽኩአል። | 146. አሸዋ ላይ የፈለሰ ቅቤ አይታፈስም። |
| 147. ሺሕሼረ ጁገል ዚትሬገዙ ቦሰአ ይዳመሳል። | 147. የአሸዋ አጥር ሲደገፉት ይፈርሳል። |
| 148. ሼለሞ ቀብሪ ኡነው፥ ኡስጡዞማኸ እለብላይ ዘዩቃው። | 148. ሼለሞ ቀብሪ ኡነው፥ ኡስጡዞማኸ እለብላይ ዘዩቃው። |
| 149. ቀልቢቤ ዛል ቁልሑወላሑ። | 149. በልብ ያለውን ይናገሩ። |
| 150. ቀርቤ መሕጀመ ቀናወቤ መሓሰስ። | 150. በቀንድ ወግቶ፥ በጅራት አባብሶ። |
| 151. ቀርና ፈቀር። | 151. ከእኩያ ጋር ይዘመር። |
| 152. ቀነኒ ወልዲ ቁይሌ ይበካል። | 152. የቅምጥል ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል። |
| 153. ቀጪን ዱፍ የምሐጠኝ ዳጂዋ ወዳጂኤው እላይባሌ። | 153. ዘመድ አዝማዴን ልለይበት ቀጭን ንፋስ ይምታኝ። |
| 154. ቀረአመ ዘዩቅ ቀሕወ ይቀድሓል። | 154. ማንበብ የማይችል ቡና ይቀዳል (ችሎታ ስላነሰው) ። |
| 155. ቁምቁምቤ ጣን ሹምቡረ ተፈጀ። | 155. በመቀንጠብ ሸከም ሸምብራ ያልቅ። |
| 156. ቁዱድቤ ቂምጪር ይማጃል። | 156. ቁዱድቤ ቂምጪር ይማጃል። |
| 157. ቂጥቤ ዳንዲን፥ ድናዲንቤ ቂጥ ዩጫል። | 157. ከሲላ ኤሲ ከኤሊም ሲሳ ይወለዳል። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 158. ቂሽነዋ ጊድራው ኣውዞ ይፋጨሐል። | 158. ቂሽነዋ ጊድራው ኣውዞ ይፋጨሐል። |
| 159. ቃሊዋ ረኺስቤም አይቅበጠነ። | 159. በውድም ሆነ በርካሽ ጊዜ ያኑረን (ምንም አይደል ዕድሜ ይስጠን) ። |
| 160. ቃሙው ቆነጦ ጊር ሳተል ቃም የሐሜል። | 160. ሲቆነጠጡ ገላን በሞላ ያሳምሙ። |
| 161. ቃም ቃምዜሌ ትበካት። | 161. ሰውነት ለሰውነት ታለቅስ። |
| 162. ቌሕ ወልዲ አቢስ በጂሕ። | 162. ቀይ ልጅ አበሳው ብዙ። |
| 163. ቌጬ ዛየ ደወ፥ አትቌጬ ዛየ እዳወ። | 163. ወደ ሥራ ሂዱ ያለ መድህኒት፥ አትሂዱ ያለ ግን ጠላት። |
| 164. ቅባጭሌ አሕሊም ኤለ። | 164. ቅባጭሌ አሕሊም ኤለ። |
| 165. ቅባጭ በጂሕ የትቅማጥራል። | 165. ማጣት ብዙ ያናግራል። |
| 166. ቅባጭቤ ርኻብ ሐልበ። | 166. ቅባጭቤ ርኻብ ሐልበ። |
| 167. ቅባጭ ነቱንተ። | 167. እጦት በሽታ ነው። |
| 168. ቅባጭ ዘዩቅ ርኻብ ዩቁሜል። | 168. እጦት የማያውቅ ማግኘትንም አያውቅ። |
| 169. ቅባባው አሐድ ጊር ጠይንተኸ ባዮ ጊር ኮአታኝ ቌሒንተኸ ይሎሜል። | 169. ምጣድን አንዴ ጥቁር ነህ ካሉት እንደገና ቀይ ነህ አይሉትም። |
| 170. ቅባጭ የትቃብጣል ርኻብ የትካሕላል። | 170. ማጣት (ድህነት) ያጣላል ማግኘት ያስማማል። |
| 171. ማጣት (ድህነት) ያጣላል ማግኘት ያስማማል። | 171. ቁንጅናን በጥብጠው አይጠጡም። |
| 172. ቆር ዘሌልባቤ ቃኙም ኤልበ። | 172. መልከ ጥፉ ዕረፍት አያውቅም። |
| 173. ቆርዜሌ ዝነሰኤው አመል ዜሌ ፈትሔ። | 173. ለመልኳ ያገቧትን ሚስት ላመሏ ፈቷት። |
| 174. ቆርዞ ሚን የቁምሲ ጠለስዞ ሚን የሕማሊ። | 174. ቆርዞ ሚን የቁምሲ ጠለስዞ ሚን የሕማሊ። |
| 175. ቆበዋ ቀብሪ ይላዮሜል። | 175. በእኩያና በመቃብር አያዳሉም። |
| 176. ቆበዞቤ ዘልቀኘአ ጋሩም አለትሔደረ። | 176. በጓደኛው ያልቀና ቤቱን አላስተዳደረም። |
| 177. በሐር ለእይቤ ይጠራዛል። | 177. በሐር ለእይቤ ይጠራዛል። |
| 178. በሐርቤ ሚይ መድሰል። | 178. ለባሕር ውሃ መጨመር (ለባሕር ውሃ አይሠፈር) ። |
| 179. በሎኝ ባይ ጉምነ ቁብዜቤ እሰጠ። | 179. እዩኝ ባይ ሴተኛ አዳሪ በተረከዟ ላይ ምልክት ይኖራል (ሂና ተረከዟን ሁሌ ስለምትቀባ) ። |
| 180. በለአም ቱመ ነከአም ቱመ። | 180. ቢበሉትም ነጭ ሽንኩርት ቢነኩትም ነጭ ሽንኩት። |
| 181. በሰር እቦችዋ ሚሽቲው ዘትካሐላንተ። | 181. ሥጋ ባልና ሚስትን ያስማማ ነው። |
| 182. በሰር ዘዩቅሌ ኩፍ ሰጦ። | 182. ሥጋ ለማያውቅ ሳንባ ሰጡት። |
| 183. በሰር ወደቀ ጊር ቁሻሽበሕ ሐፍ ይላል። | 183. ሥጋ ቢወድቅ ከቆሻሻ ጋር ይነሳል። |
| 184. በረሕቲ ዜገ ያሻል። | 184. ርህራሄ ያደኸያል። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 185. በቀሉው አውኸሸ ማንተባዬ ጊር ካኬ ፈረዝ ባቲ። | 185. በቅሎን አባትሽ ማን ነው ቢሏት አጐቴ ፈረስ አለች። |
| 186. በናን ጋርዱሙሳንዱሙስ። | 186. የግንበኛ ቤት የፈራረሰ። |
| 187. በለቹ ኣሾ ጊር አብዱላሒ ሳዲቅ ኩት አልሾ ጊር ከቢር ሓሚድ ኩት። | 187. ቢደግሱ እንደ አብዱላሂ ሳዲቅ፥ ባይደግሱ ግን እንደ ከቢር ሓሚድ (አብዱላሂ ሐብታም ስለነበሩ ሀገሬውን በሙሉ ደግሰው ሲያበሉ ከቢር ሓሚድ ግን ድሀ በመሆናቸው ያለ ሠርግ ልጃቸውን ስለዳሩ ነው) ። |
| 188. በኺል ዲነትዞ በኸቲ። | 188. የቆንቋና ሀብት ይበክት። |
| 189. በኺቲ ዛልበ እታይቤ ወራሰ ይትቀበጡሜል። | 189. ጥንብ ላለበት ጅብ አያጡም። |
| 190. በኸቲ ኣውዞሴ ሶር። | 190. በክት ለባለቤቱ ተስማሚ ምግብ። |
| 191. በድሪ እያም ዘትቢራጀ። | 191. በዕለት በድሪ (በረመዳን 17ኛው ቀን) የተደናገረ። |
| 192. በጂሕ ስናን ሐለኝ ባይ ትቤ ጥቀሾ ድላገ ሐለኝ ባይቲ ይማጃል። | 192. ብዙ ነገር አለኝ ከማለት ትንሽ ሥራ አለኝ ማለት ይሻላል። |
| 193. በጂሕ ዮሎሖል ብላይ በጂሕ የቢኖሜል። | 193. ብዙ ይበሏል እንጂ ብዙ አይናገሩም። |
| 194. በጂሕ ቱደኝቤ ጥቀሾ ፍረኝመ እግድረኝ። | 194. ብዙ ከምትወደኝ ጥቂት ፈርተህ አክብረኝ። (ሰውን መናቅ አያስፈልግም ለማለት ነው) ። |
| 195. ቡርሓነሴ ረገዞ ሑርጉመር። | 195. የሠርዶ ምስክር እንግጫ (የአይጥ ምስክርዋ ድንቢጥ እንደሚባለው ነው) ። |
| 196. ቡቺው በለቹዜቤ ቀበጤ። | 196. ውሻን ሠርግ ዕለት ከቤት አጧት። |
| 197. ቡቺ ውሕ ዘተልበኸ ኩት ኒፍጫጭ ጊኘሎ። | 197. ውሻ እንዳትጮህብህ ልፋጭ ጣልላት። |
| 198. ቡቺ ዝጠለቂው አቱሸነ። | 198. ውሻ የለከፈውን ገበታ አታድረገን። |
| 199. ቡቺ ዝሐነቂውው ዩዳል። | 199. ውሻ ያነቀውን ይወዳል። |
| 200. ቡቺ ዘሌቂውው ይረሱሜል | 200. ውሻ ያሳደገውን አይረሳም። |
| 201. ቢሚይ ዘለምድቲ ቢመረኸ ቡቲ። | 201. በውሃ የለመደች መረቅ ውስጥ ገባች። |
| 202. ባለጌ አይዘው አልወድሸኙም ይላል። | 202. ባለጌ እናቱን አልወለድሽኝም ይላል። |
| 203. ባለጌ ዘልመሐጦቤ ይበካል። | 203. ባለጌ ሳይመቱት ያለቅሳል። |
| 204. ባረ ኢን ዞሐጥትመ ጋሚለ ኢንሌ ቲትማሐጥዛት። | 204. ባረ ኢን ዞሐጥትመ ጋሚለ ኢንሌ ቲትማሐጥዛት። |
| 205. ባረ ኢን ዞሐጥትመ ጋሚለ ኢንሌ ቲትማሐጥዛት። | 205. ባረ ኢን ዞሐጥትመ ጋሚለ ኢንሌ ቲትማሐጥዛት። |
| 206. ባው አነቴው ጊር ሐምዲ ሚስኪን ሞተ ጊር መቺይ ሎሖል። | 206. ሃብታም ቢታመም ይመስገን፥ ድሀ ቢሞት መች ይሿል። |
| 207. ባዩኝ ባይቲ በሉኝ ባይቲ ንተ። | 207. አሉኝ ማለት በሉኝ እንደ ማለት። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 208. ባዮዋ ባይቲ ተናሰኡመ ኤሉመው ወለዱ። | 208. አሉባልታን አግብቶ የለምን ወለዱ (ለወሬ የለውም ፍሬ) ። |
| 209. ባዴ ወራብ የብለአኝ። | 209. የሀገሬ ጅብ ይብላኝ። |
| 210. ባድ አላው ይራል። | 210. ሀገር አላህን የመለከታል ሰጪም ነሺም እርሱ ነው። |
| 211. ተልቃላቂው ጪንቂ ገደሌው። | 211. ተቀላቃይን ጪንቅ ገደለው። |
| 212. ተስትዋ ከፍቲ ጢሚጃን ተዩ። | 212. ደስታና ሐዘን ጥንድ ናቸው። |
| 213. ተዝነበለ ብላይ አልቲቀድሓም። | 213. ዘንበል እለ እንጂ አልተቀዳም። |
| 214. ተጉግ ሐጠቦ ጊር ሲበ ዩኹ ኑሜል | 214. ጐተራ ቢያጥቡት ጋን አይሆንም። |
| 215. ቱመ ወልዲ ቱምባኽ። | 215. የነጭ ሽንኩት ልጅ ቱሃን (ሁለቱም ስለሚገሙ) ። |
| 216. ቱጃር ዴረ ኣሚን ዛጥ። | 216. የሀብታም ጓዳ የታማኝ። |
| 217. ቱፍ ዛዮ ምራቅቤ ይርገብ ኑሜል። | 217. የተፉትን ምራቅ አይልሱትም። |
| 218. ትበክ ትበኬይ! ቢጢር ኸቢ፥ ቢጢዞው ቅበጪመ ሐርቱ ሕጀሪ። | 218. አልቃሽ ሆይ! እንጐቻ አግኝ እርሱንም አጥተሽ ባዶ ሆድ እደሪ። |
| 219. ትበክ አሩዝ ትኸሸ አሩዝ። | 219. ታለቅስ ሙሽራ ትሻ ሙሽርነት። |
| 220. ነቢ ኑሕ ኩረ። | 220. የነቢይ ኖሕ አሞራ (የቁራ መልክተኛ) ። |
| 221. ነለኽ ሰላመ ዛልበ ጋረ። | 221. ሰላም ልበል ገንዘብ ያለበትን ቤት (ሰዎች አንድ ጥቅም የሚያገኙበትን ቤት ያዘወትራሉ) ። |
| 222. ነቢ ወር ዲጃ ጊር እስሓበ ወር ቀረ። | 222. የነቢይ ወሬ ሲነሳ (ሲመጣ) የሐዋሪያ ይቀር። |
| 223. ነአኡሎ ጊር ዘላቀ ነከአ ጊሩም ዩቁሜል። | 223. ነገርን ነካ ሲያደጉለት የማያውቅ ቢነኩትም አያውቅ። |
| 224. ነቱሌ ጢትዋ ጊዲሩም ኤለ። | 224. የበሽታ ትንሽና ትልቅ የለውም። |
| 225. ነደበ ኢርዛት ከርሳምነት ቃም ኢርዛት ቅባጭ። | 225. የመደብ (መቀመጫ) መታረዝ ሆዳምነት፥ የገላ መታረዝ እጦት። |
| 226. ነዲ ቡሉኸ ኢንዞ ጡፉእ። | 226. የመጀመሪያ ጉርምስና እውነት (ብዙውን ጊዜ በራሱ ለመመራት እውቀቱንና ጉልበቱን ለማሳየት እና ለሕግ ላለመገዛት ስለ ሚሞክር ነው። ሆኖም ጓደኞቹ የሚያደርጉትን ሳያመዛዝን ሲያደርግ ይታያል። |
| 227. ነፍሲ ዲጃ ጊር ነፌስ ቀረ ወልዲ ዲጃ ጊር ዋሊድ ቀረ። | 227. ጭንቅ ሲመጣ (የነፍስ ነገር) የሚወዱት ይቀር ልጅ ሲመጣ ወላጅ ይቀር። |
| 228. ነፍሲሌ ዛዮ ዱስ እለገሌ ዛዮ ሹንኩርተ። | 228. ለራስ ያሉት ማር ለባዕድ ያሉት ሽንኩርት። |
| 229. ኑር በሉኝ በሸማ። | 229. ኑር በሉኝ በሸማ (አሚር ኑር በሸማ ኑር በሉኝ ያሉት አንድ ቀን ሠርግ ቤት ተጠርተው የተበጣጠሰ ልብስ ለብሰው ሲሄዱ አጋፋሪዎቹ ሳያውቁ ከበር ላይ መለሱአቸው ወደ ቤታቸው ተመልሰው የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ሲመለሱ ግን በክብር ተቀብለው አስተናገድአቸው።ምግብ ሲቀርብ ከመብላት ፈንታ ልብሳቸውን መቀባት ጀመሩ ለምን ይህን |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| | እንደሚያደርጉ ሲጠየቁ ለዚህ ክብር ያበቃው ልብሴ ነው እንጂ እኔማ መጥቼ ከበር ተባረርኩ አሉ ይባላል) ። |
| 230. ናሙስ ቅራረቲንተ ይቂርሖ ይኸሻል። | 230. ክብር መስተዋት ነው ይጠብቁት ይሻል። |
| 231. ናሙስ ኻዱው አውዞ ይቂርሐሐል። | 231. የራሱን ክብር የሚጠብቀው ባለቤቱ ነው። |
| 232. ንጃቱው ዱስዜሌ ይቀብጤሐል። | 232. ንብን ለማርዋ ይተዋቷል። |
| 233. አሐድ ሳቅ ዘሌላው ጋሚስ ጡኡን አመለጤው። | 233. አሐድ ሳቅ ዘሌላው ጋሚስ ጡኡን አመለጤው። |
| 234. አሐድ ሙጢ ዛለ ቲከ ይልዛል ይሙታል። | 234. አንድ ብቻ ያለው ያችኑ ሲያባርር (ሲጠብቅ) ይሞታል። |
| 235. አሐድ አየትቁበጢ። | 235. አንድ አያሳጣ። |
| 236. አሐድ ኢን ዛለ አፊር አፊር ያሹሜል። | 236. አሐድ ኢን ዛለ አፊር አፊር ያሹሜል። |
| 237. አሐድ ኢጂ ወሰኸ ያጬሜል። | 237. አንድ እጅ እድፍ አያወጣም። |
| 238. አሐድዞ መርመርሜ ይቃኖመ አሐድዞ መርመርቤቾፍ ይሎሖል። | 238. በአንዱ ትከሻ ቆሞ ወደ ሌላው ይዘሏል። |
| 239. አሐድ ያም በለቹ ወልዲም አለሌቀ። | 239. የአንድ ቀን ሠርግ ልጅ አላሳደገም። |
| 240. አሐድ ገዱቤ ወራበ ኮአት ጊር ይነኸሱሜል። | 240. ባንድ ጉድጓድ ሁለቴ ጅብ አይነክስም። |
| 241. አሕሊ መገረዞ አመት አለገ መገረዞ ዚአበድ። | 241. የዘመድ ጥል ለዓመት የባዕድ ጥል ለዘለዓለም። |
| 242. አሕሊ ስናንዋ ጣይ በሰር የበርዶ ይኸሻል። | 242. አሕሊ ስናንዋ ጣይ በሰር የበርዶ ይኸሻል። |
| 243. አሕሊዋ ሊሕዲ እለገዋ ኡገ። | 243. ዘመድና መቃብር ባዕድና መንገድ (ዘመድን እስከ ፣መቃብር ባዕድን እመንገድ ያገኙዋል) ። |
| 244. አሕሊ ኩም አዳወ አየግኙሎ ደወ። | 244. ለዘመድ ጠላት አያገኙለት መድሃኒት። |
| 245. አለ መከሪዞ ዲጀ ጊር ኡሱእ መከሪዞ ቀረ። | 245. የአላህ ብልጠት ከመጣ የሰው ይቀር። |
| 246. የአላህ ብልጠት ከመጣ የሰው ይቀር። | 246. የአላህ ብልጠት ከመጣ የሰው ይቀር። |
| 247. እለገ ቢኪትዞ አላ ቀብሪ አፍ። | 247. የባዕድ ለቅሶ እስከ መቃብር። |
| 248. አለገ ብሎት አመረ ብሎት። | 248. ባዕድ የበላው አሞራ የበላው። |
| 249. አለጋው ረገሌ ቀበጦ። | 249. አለጋው ረገሌ ቀበጦ። |
| 250. አሊሌ ዛዮ እለዊሌ ኻነ። | 250. ለእሊ ያሉት፥ ለአለዊ ሆነለት። |
| 251. ለእሊ ያሉት፥ ለአለዊ ሆነለት። | 251. የአሊን ጋሻ ያነገተ፥ አብዳል ለጭፈራ ወረደ (አብዳል የቦታ ስም ነው) ። |
| 252. አልቀኔ ቂጪቢው ሳኺእ (ሳኒእ) ቶየቤ ዝበቂልቲው። | 252. በሠራተኛ ሠፈር የበቀለችው ቁልቋል አልቀናት። |
| 253. እልበቀ አልቢቃቀ ጣይ ሲጃጀ። | 253. ከበግ ቆዳ የተሠራው መስገጃ አይበቃ አይብቃቃ። |
| 254. አልቡሱል የበሰላል ኩሳር በሶ ወዞነ የበስላል። | 254. ያልገራ (ጥሬ) ያደከማል የድንብላል በሶ ልብ ያቆስላል። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 255. አልእማኖት ሐራስ ኢጂቤ ሹር የቲሻል። | 255. አላምን ያለች አራስ ታገነፋ ለራስ (ለራስዋ ታገነፋለች) ። |
| 256. አላምን ያለች አራስ ታገነፋ ለራስ (ለራስዋ ታገነፋለች) ። | 256. ፈቃደኛነት ከሌለ የገብስ አከርማም አይነቀል። |
| 257. አልደላጊ ነደበ ገዳለ። | 257. ሥራ ፈት መደብ ላይ ይውላል (ይገድላል) ። |
| 258. አልዛኘ ጊር ምሼት። | 258. ካልነጋ ምሽት። |
| 259. አልገዘአመ አው አልወለደመ አልርኡሎ። | 259. ወልዶ ወይም ሀብት አፍርቶ አልታየ (ለት) ። |
| 260. አመልቤ ሽሪፍነቱው። | 260. በአመል ሽሪፍነትን (መከበርን) ። |
| 261. አመልዋ ኪዙው መቴነስዞ ይማጃል። | 261. አመልንና ውሸትን ማሳነሱ ይበጃል። |
| 262. አማንነትቤ ዘበላው ዲርቂ | 262. በጥሞና እምቢ ያለን ኃይል ያስጠዋል። |
| 263. አምበ ዘሌለ ያኢም ኤስ። | 263. ጐረቤት የሌለው አምባጓሮ የለው። |
| 264. አረብ ደንተዞሌ ከኒፍ ጠረገ። | 264. አረብ እንዲቀናው (ለደንታው) የሠገራ ጉድጓድ ጠረገ። |
| 265. አኑዚት ቢዴረ ወርዜ ቢቃጪ። | 265. ሙሽራ በጓዳ፥ ወሬዋ ግን በሜዳ። |
| 266. አራት ሲብሐዞው ኡሩስ በሰር አታይቤ ኣረዶ። | 266. ስብን ምላስ በራስ ሥጋ አጠገብ ያኖሩታል። |
| 267. አራትዋ ሲንዞ ይትናኽሳሉ። | 267. ምላስና ጥርስ አንኳን ይናከሳሉ። |
| 268. አራቴይሩሴው ቁርሒኙ። | 268. ምሳሌ ሆይ (ራሴን) ጠብቂኝ። |
| 269. አርጐበ ባረ ኮእት ገረበ የሐርሲዛል። | 269. በሁለት በኩል የሚያርስ የአርጐባ በሬ። |
| 270. አሱው በርበሪ አትፋለሴው። | 270. ድልህን በርበሬ አስመሰገነው። |
| 271. አሺን ዛልባ ጋሩው እሺን ዩቀሐል። | 271. ጫማ ያለበት ቤት ጫማ ያወቀው (ወንድ ያለበት ቤት ወንድ ያውቀው። ድሮ በአደሬዎች ዘንድ እምብዛም ሴቶች ጫማ አያደርጉም ነበር።) |
| 272. አቅሊቤ አቅሌል ኪሲቤኩስኩስ ዩሎሖል። | 272. በብልሃት ይበላል ጥሩ ጥሩ ምግብ በካሳ ይበላል ፓስቲ። |
| 273. አባርሴ ድናዲን ዩሎሜል። | 273. ለረሀብ ኤሲ አይበሉም። |
| 274. አቦች ክርስቲ ሳቲ ጣቁት ሐስ። | 274. የወንድ ሆድ ሰባት ማስቀመጫ ሥፍራ አለው። |
| 275. አቦችዋ ሚሽቲ ከፈኒን ተዩ። | 275. ባልና ሚስት ከፈንና ገላ ናቸው። |
| 276. አቦች ዝጠፈ ሰአ ሚይ ቀጠነ ይላል። | 276. ባል ሲጠግብ ውሃ ቀጠነ ይላል። |
| 277. አቦችዜቤ ዚትሜቼ ቢዴረ ትሰልሓት። | 277. በባልዋ የተመታች ሴት ጓዳ ገብታ ትደንሳለች። |
| 278. አቦች ጉድ መሪ አቦችንተ። | 278. ባል የመጀመሪያ ባል ነው። |
| 279. አተር ቀረ ጊር ፈስ ቀረ። | 279. አተር ቀረ ቢሉ ፈስ ቀረ። |
| 280. አተዋቅ ሩሕዚሌ መሽሕ አጭቲ። | 280. ዶሮ በራስዋ ላይ ቢላዋ አወጣች። |
| 281. አንንቱው ሺርዋ ገርብትሌ ኸለቁው። | 281. አንገት የተፈጠረው አዙሮ ለማየት። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 282. አኻኽ ኩዛል አበ ወራበሌም ሐለ። | 282. ለጅብም እንዳንተ ያለ ወንድም አለው። |
| 283. አኻኽ በሕ ኡገ ዘይሌጥ ወጨረ አየጣነኽ። | 283. ካንተ ጋር ጉዞ የማይሄድ አህያ አያጫጭንህ። |
| 284. አኽ ባዮም ደም ቱፍ ባዮም ደም። | 284. አክ ቢሉም ደም ቢተፉም ደም። |
| 285. አይቂርበኝ ዛየ ኡገቤ ቀረ። | 285. አይቅርብኝ ያለ እመንገድ ቀረ። |
| 286. አደብ ዘሌላሌ ቆጠል ሐለባማ። | 286. ሥነ ሥርዓት ያጣ ሰው አለንጋ ድርሻው። |
| 287. አደብ ዘሌላሌ ኡጋም ኤስ። | 287. ሥነ ሥርዓት ለሌለው መንገድም የለው። |
| 288. አደብ የሰጠነ ባይቲ ጊዲር ዱዋእ ኢንተ። | 288. ሥነ ሥርዓት ይስጠን ማለት ትልቅ ምርቃት። |
| 289. አዱሩም ሸሪፈንቴ። | 289. ድመትም ክብር አላት (ለክብር ከተባለ) ። |
| 290. አዱሩ ኢምቡጥ ኣጭቲ ሸቅለን ሻንኬት ኤስብቲ። | 290. ድመት አፍንቻ አወጣች ሸቅለን (የሰው ስም) አምባር አደረገች (ድሮ የማታገኘውን በማግኘቷ ኩራት ለተሰማት የሚተረት ነው።) |
| 291. እዱሩ ደንፈዜ እላ ዴረበሪ፥ ቡቺ ደንፈዜ እላ ከተንበሪ። | 291. የድመት ድንፋታ እስከ ጓዳ፥ የውሻ ድንፋታ እስከ በር። |
| 292. «እገበሪ መቄጫም እይዋል፥ አኑውም አይኼጀኝ» ባቲ። | 292. «ከብቶች እቤትም አይዋሉ እኔም አይርገጡኝ፥» አለች። አንዲት የሐረር ንግሥት በከተማ በር ላይ ተኝታ ከብቶች ለግጦሽ ከከተማ ውጭ ይሰማሩ እኔን ግን አይርገጡኝ ብላ አዘዘች። |
| 293. አገኘ በለ (አ)፥ እሴነነ ረሰ/ እ/። | 293. አገኘ በላ፥ ተናገረ ረሳ። (ቃሉን ለማያከብር ሰው የሚነገር) ። |
| 294. አገኞ ጊር ሱብሒን ይማጅ ቀቦጦ ጊር ሰብሪን ይማጅ። | 294. የሚበላ ቢገኝ ጠዋት ቢያጡ ግን ትዕግሥት። |
| 295. እጣቢኘሌዞ ለእያ ተሐይ ሐለ። | 295. ከጣት ጣይ ይበልጣል። |
| 296. ከጣት ጣይ ይበልጣል። | 296. ጣትን ገማች ብለው ቆርጠው አይጥሏትም። |
| 297. አፈር ውስ፥ ጣቅ ለእይ ስላት። | 297. አጉል ውስ፥ በፈርስ ላይ ጸሎት (ሰው ለጸሎት መተጣጠብ) ። |
| 298. እፍዛላው እፍዘው ወኸበ። | 298. አፈኛን አፉን ግዙት። |
| 299. አፍዞ ብረት ጋር ይማግዲ ዛል። | 299. አፉ የብረት ቤት የሚያቃጥል። |
| 300. አፍጐን ዘሌላሌ እራዙም ኤለ። | 300. ቡትቶ የሌለው ልብስ የለው። |
| 301. እፍሴ ከራቱም ኤለ። | 301. አፍ ዳገት የለውም። |
| 302. ኡሩስዞው ዘይጦር እንገቱም ኤል። | 302. ራሱን የማይሸከም አንገት የለም። |
| 303. ኡሱእ ረቀ ሐጀ ጊር ይሙታል። | 303. ሰው ሞኝ ነው ቢወጉት የሚሞት። |
| 304. ኡሱእ ኢጂቤ እሳት ይማግዱሜል። | 304. በሰው እጅ እሳት አይፋጅም። |
| 305. ኡሱእ ዘሌላሌ ኡሱእነቱም ኤለ። | 305. ዘመድ የሌለው ከሰውነት የራቀ። |
| 306. ኡሱእ ደም ይከልሓል። | 306. የሰው ደም ይጣራል (ምንም ቢዘገይ ነፍሰ ገዳይ ይገኛል) ። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 307. ኡሱእ ዝሐተፌውቤ ዘመን ዝሐተፌው ይማጃል። | 307. ሰው ከመከረው ዘመን የመከረው። |
| 308. ኡሱእ ፈትቤ መቃነን እዛብንተ። | 308. መለመን ሲአል ነው። |
| 309. ኡሱእሌ አይኩ የኸኖ ኡሱእ ብላዩም አይኩ የኸኖ። | 309. ለሰው ምን ይኮናል? ያለ ሰውም እንዴት ይኮናል?። |
| 310. ኡሱእሌ ኡሱእሙራ የትዞ። | 310. ሰው ለሰው መስተዋቱ። |
| 311. ኡሱእ ዘልፈረ እላው ይፈሩሜል። | 311. ሰውን ያልፈራ አላህንም አይፈራ። |
| 312. ኡሱኽ ኡስጡ ኤስድ። | 312. የእሾህ መሃል አበባ። |
| 313. ኡሱኹው ኡሱኽ ያጨሐል። | 313. እሾህን እሾህ ያወጣዋል። |
| 314. ኡንሌ ኢኑም ኤለ። | 314. ለድንጋይ የለው ዓይን። |
| 315. ኡንቀቤ ኡን ሐልበ። | 315. ቆሎው ጠጠር አለው። (ለማይታመን ነገር የሚባል) ። |
| 316. ኡንቤ ለሒጥ መፋጨ። | 316. ከድንጋይ ልጣጭ መፈለግ። |
| 317. ኡንዋ ቁሉአ ይትፋለቁሜል። | 317. ድንጋይና ቅል አይፍናከቱም። |
| 318. ኡኻት ኻዱው መብረድመ መብለእ ይማጅ። | 318. እንጀራን አቀዝቅዞ መብላት ይበጃል። |
| 319. ኡኻት ጊዲሪንተ። | 319. እንጀራ ትልቅ ነው። |
| 320. ኡዙኑው ቆቾ ጊር ኑዱልዞ ይቀራል። | 320. ጆሮን ቢቆርጡት ቀዳዳው ይቀራል። |
| 321. ኡዙን ኡመዜባሕ ቀርኒ። | 321. ጆሮ ከአያቷ ጋር እኩያ ናት። |
| 322. ኡገቤ ኹፊ ጪጪጭ፥ ጋርቤ ረሐብ ቁቆቅ። | 322. እመንገድ የጫማው ድምጽ ያምር፥ ከቤት ግን በረሐብ ይማቅቅ። |
| 323. ኡፉው መሐጤ ጊር ኢንት በካተ። | 323. አፍንጫን ቢመቱት ዓይን ያለቅሳል። |
| 324. ኡፉው መቆመጨ እፍ ሜሰብ 1። | 324. አፍንጫን ቆርጦ አፍ ማድረግ። |
| 325. ኡፍ ኡፍ ወልዲ አለሌቃም። | 325. እፍ እፍ ማለት ልጅን አላሳደገም። |
| 326. ኡፍሌ ዝሶቻው እፍ ይስቦሐል። | 326. ለአፍንጫ የሸተተውን ወደ አፍ ያስገቡዋል። |
| 327. ኡፍ ኢንፊጥ እፍ አይቦእ። | 327. የአፍንጫን ንፍጥ አፍ አያስገቡም። |
| 328. ኡፍ ይስድሌ ዘትጌቦ ወንደቅ ኡን የቂብለ እትጌበለ። | 328. ወፍ ሊያሳድድ የተቀጠረ ድንጋይ የሚያቀብል ቀጠረ። |
| 329. ኢርቤ ኢጂ ሞረድ። | 329. ፀሐይን በእጅ መከለል። |
| 330. ኢር እሳል ዘላረዶው ዝመሽ ሰእ የገኞሜል። | 330. ፀሐይ እያለች ያላስቀመጡትን ሲመሽ አያገኙም። |
| 331. ኢር እሳል ዝመሸቤው አቱሸርኒ። | 331. ፀሐይ እያለች የመሸበት (አታድርገን) ። |
| 332. ኢሺሽ ዞለኡቡ ኢጂቤ ሐመድ የሐፍሱቦሐል። | 332. ቅቤ ባበሉበት እጅ አመድ ያፍሱበት። |
| 333. ኢኔይ ትሬየ ኡዙኔይ ትሰማየ ዛዮው ታብሌየ ሴነትበኬየ። | 333. ዓይኔ እያየሽ ጆሮዬ እየሰማሽ የተባለውን እምቢ ብለሽ፥ የጸጸት ለቅሶ ታለቅሻለሽ። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 334. ኢን በለሑው ከልከ በለሕ ቀድሜው። | 334. ስለት ያለውን ዓይን ስለት ያለውን መጥረቢያ ቀደመው። |
| 335. ኢን ላዮመ አፌት ባዮ። | 335. ዓይን ብሎ ድህነትን ይሏል። |
| 336. ኢን ዘሌለ ሺኢሽቲ ኻኡ ቡኝ ጊር ቆንጡኝ ባየ። | 336. ዓይነ ስውር ሶስት ሰዎች ካሉ ቅንጥጡኝ አለ (ሶስት ሰው ባለበት ሥፍራ ሌላውን ካሙ ከሶስቱ አንዱ ለሚታማው ሰው ምናልባት ዘመድ ሳይሆን አይቀርም በሚል ነው።) |
| 337. ኢን ዘልቶየ ቀልቢ ዘለፎየ። | 337. ዓይኑ በየመንገዱ የሚንከራተት ልቡ አንድ ቦታ የማያድር። |
| 338. ኢንዞቤ ዚትሔወስ ሚይሌ መላም ኤለ። | 338. ከምንጩ ለደፈረሰ ውሃ የለው መላ። |
| 339. ኢንዶችዋ ዊጅ ሐፍ ያሸዛል ስናን ይበርዱሜል። | 339. ሴትና ልጅ የሚያስነሱት ነገር በቀላሉ አይበርድም። |
| 340. ኢንዶቹው ስንዱቅኻው አቱሬ። | 340. ለሚስትህ ሳጥንህን አታሳይ። |
| 341. ኢን ዘሌላው በርቲ መጤመስ። | 341. ዓይነ ሥውርን ምርኩስ መቀማት። |
| 342. ኢንዶች እቦችዜሌ መሐለ ቅንቴ። | 342. ሚስት ለባልዋ ገንዘብ ናት። |
| 343. ኢንዶችዋ ዳግቤ ይትራወ ጦሜል። | 343. በሴትና በዳገት አይሮጡም። |
| 344. ኢንጪ «ብረቱም እልቆጬኝ ኢንጪተ ብላይ» ባየ። | 344. እንጨት «የቆረጠኝ እንጨት ነው እንጂ ብረት አይደለም» አለ (በእንጨትና በብረት የተሠራውን መጥረቢያ ማለቱ ነው) ። |
| 345. ኢንጪ ዘላጨቤ ቆጢዛጨ። | 345. ከእንጨት በፊት (ሳያድግ) ቅጠል ያወጣ። |
| 346. ኢጂ አፉው የሙሳሜል። | 346. እጅ አፍን አይስትም። |
| 347. ኢጂቤ ሲጥ ኢጊርቤ ፋጭ። | 347. በእጅ ስጥ በእግር ፈልግ። |
| 348. ኢጂቤ በርቲ ኡሩስቤ። | 348. በእጅ በትር በራስ ብልሃት። |
| 349. ኢጂቤ ዛሾ ኩሑል ኢንየጠፋል። | 349. በእጅ የኳሉት ኩል ዓይን ያጠፋል። |
| 350. ኢጊር እሺን ነደበ እይትሴቀል። | 350. ጫማን መደብ ላይ አያወጡም። |
| 351. እለ ዘዩቅል ሲር ስጦ በሶር ዘዩቅሌ ኩፍ ስጦ። | 351. አገዳ ለማያውቅ ስር፥ ሥጋ ለማያውቅ ሳንባ ይሰጧል። |
| 352. ኣረዶ ሞት ሰቀሎ ገበተ። | 352. ቢያስቀምጡት ስፌድ፥ በግድግዳ ላይ ቢሰቅሉት ገበቴ (ቆሪ) (እንዳደረጉት የሚሆን ሰው) ። |
| 353. አርቤ ሙት ይማጅ የገሲሱምቤ ቀብሪ ይማጅ። | 353. ከውርደት ሞት፥ ከመጥፎ ስም መቃብር (ይሻላል) ። |
| 354. ኣቂሌ ንኩኡሎ፥ ረቀሌንደሉሎ። | 354. ለብልህ ያስታውሱ፥ ለሞኝ ግን ይኮረኩሩ። |
| 355. ኣንዋ እኻኽ ዘር ሚይዋ ዝናብ ሚይንተነ። | 355. እኔና አንተ የዝናብና የወንዝ ውሃ ነን። |
| 356. አንኩት ኹንኑ ባይቲ ጅናም ኹኑ ባይቲ። | 356. እንደኔ ሁኑ ማለት እበዱ ማለት። |
| 357. ኣንሌ ሑሬይ ኡሱእሌ ፉሬይ። | 357. ለኔ ቆንጆ ለሰው ግን አይጥ። |
| 358. ኣዌ ሚሽቲው እያ ባኺ ጊርሑሉ የምሰሌ። | 358. የእንጀራ እናቴን እማማ ስላት እውነት መሰላት። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 359. ኣዌውረእኾ ጊር እው መየ እገሰሴኝ፥ ኡሜው ሪእኼ ጊር ሰሐቅ ገደሌኝ። | 359. አባቴን ባየው አባ መየን አስናቀኝ፥ የሴት አያቴን ባያት ሳቅ ገደለኝ። |
| 360. ኣው ኸጢብ ዛለዩቤ ይኺ ጥባሉ። | 360. ሰባኪ ባለው ይሰብካል። |
| 361. ኣውሚሽቲ ኣይ አትኹን ኡንቀ ሕራት እይኹን። | 361. የእንጀራ እናት አትሁን። ናት፥ ቆሎ አይሆን ራት አይሆን። |
| 362. ኣው ሰሪ ኢንጪንተ። | 362. አባት የዱር እንጨት (ማታ ወደ ቤት ስለሚገባ) ። |
| 363. ኣው አባዲር ኢጊርዝዩ ጉሙል ኢንተ። | 363. የኣው አባድር እግር የታጠፈ ነው (ጥጋብ አያዋጣም አደብ ይሻላል ለማለት ነው) ። (በሐረር የታወቁ የታሪክ ሰው) ። |
| 364. ኣው እሳል እዜር፥ ኣይ እሳልቲ ኢኺስተ። | 364. አባት እያለ አጐት፥ እናት እያለች አክስት (አይታጡም) ። |
| 365. ኣልቂ ቢኢሻረ። | 365. ለብልህ ያመልክቱ። |
| 366. ኣውመ የሐርሲ ወልዲመ ይማሕሲ። | 366. አባት ያርስ፥ ልጅ ግን ያፈርስ (ያበላሽ) ። |
| 367. ኣው ወልዲ ከራ ወልደየ። | 367. የአባት ልጅ የወልዲያ መንገ (የወልዲያ መንገድ አስቸጋሪ ነው) ። |
| 368. ኣውዞ ላምገፍቤ ዝመሐጤው ባራው፥ አለገ ኡንቤ ይመራሕጠል። | 368. ባለቤቱ በኩበት የመታው ገበሬ ባዕድ በድንጋይ የመታዋል። |
| 369. ኣውዞ ዘቄሼው ቡቺቤ ኩሉዞም ኢጂ ያርድበሐል። | 369. ባለቤቱ ባጥላላው ውሻ ሁሉም እጁን ይሰነዝርበታል። |
| 370. ኣውዞ ዞደዴውሌ አንቀርደወ። | 370. ከፈቀደው አባቱ ጨጓራም መድኃኒቱ። |
| 371. ኣዩው ጥሎት፥ ወልዲው ኸተረ ስሞት። | 371. እናትዋን ጥላቻ የልጅዋን ስም አጐደፈ። |
| 372. ኣይ ሻብ ፋጥ ሹንኩርተ ንቀል እብቂል። | 372. የኣይ ሻብፋጥ ሽንኩርት ተነቅሎ የሚተከል (ባንድ ነገር የማይረጋ) አይሻብፋጥ የተባሉት ሴት ሌላውን ሰው ካለማመናቸው የተነሳ ሽንኩርታቸውን ጠዋት አብቅለው ማታ ወደ ቤት ሲሄዱ ነቅለው ቤታቸው ይዘው ይሄዱ ነበር ይባላል። |
| 373. ኣይዋ ሚይሌ ግሳቱም ኤለዩ። | 373. ለእናትና ለውሃ መጥፎነት የለውም። |
| 374. ኣይ ጦትዜኩት ኮኦት ቱኹ ኑሜት። | 374. እናት እንደጡትዋ ሁለት አትሆንም። |
| 375. ኣይ እሳልቲ ቀድረዜው ዩቄሜል። | 375. እናት እያለች ዋጋዋን አያውቁም። |
| 376. ኣጥ ዱፍንሴም ሐቡ ኤለ። | 376. ለሁሉም አጥንት የለው መቅን። |
| 377. እሳቱው ዝማግዴው ዩቀሐል። | 377. እሳትን የሚያውቀው ያቃጠሰው። |
| 378. እሳትን የሚያውቀው ያቃጠሰው። | 378. የቤተሰብ ስም የሌለውን ሰው እጓዳ ስፍራ ቀበሩት። |
| 379. እመልማነ ቢኪት ኢን ኑር የናቅሳል። | 379. ከመጠን በላይ ማልቀስ የዓይን ብሌንን ያጠፋል። |
| 380. እመልማነ ሰሐቅ ቀልቢ የደርቃል። | 380. ከመጠን በላይ ሳቅ ልብ ያደርቅ። |
| 381. እመትንሰእ ግዘእ እመት ውለድ ብለእ። | 381. ሚስት ሳታገባ ሐብት አፍራ፥ ልጅ ሳትወልድ ብላ። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 382. እመትውለድ ብእሰ፥ ኢስ ወለድኺ ቤሑርሴ ቁኒቤ ወሐጥ። | 382. ሳትወልድ ብላ ከወልድክ ወዲያ በቁምህ ዋጥ። |
| 383. እመየሎ ይላል፥ እላል ለሚ አጢዞ የቀድማል። | 383. ሳይናገሩት ይናገራል፥ እሳል ለሚ (ስም) ራሱ ያስቀድማል (ጅራፍ ራሱ ገርፎ ይጮኻል) ። |
| 384. እመይተርፌ ዘሌቀሕቲ እሰይገቤ ሞቲ። | 384. ሳይተፋት ያበደረች ሳይመለስላት ሞተች (ብድሩ) ። |
| 385. እመይኹን መገን ኢስኻነ ቤሑርሴ መገንታም ኤለ። | 385. ሳይሆን እቤት፥ ከሆነ ወዲያ ግን እቤት አይሉም። |
| 386. እስይጠርሖ ለቤክ። | 386. ሳይጠሩት አቤት። |
| 387. እራዝ ዝገኘ ጅናምቤ እራዝ ዘልገኘ ይበዝሐል። | 387. ልብስ ከጣለው ዕብድ፥ ልብስ ያልጣለው ይበዛል። |
| 388. እሳትዋ ሚስኪን ይንካኮ የኽሹሜል። | 388. እሳትና ድሃ ሲነካኩት አይወድም። |
| 389. እሼትቤ ዝጄካው እሼትቤ ኡሱኽ የሐጀ። | 389. መሬት በቀስታ የረገጠ ሰው በቀስታ እሾህ ይወጋው። |
| 390. አላኽዋ እበላኽ ይትካሐ ሉሜል። | 390. አበላለሁና እበላለሁ አይስማሙም። |
| 391. አላኽቤ መትበለእ ሐልበ። | 391. እበላለሁ በማለት አለበት መበላት። |
| 392. አርዝኻነ ኡሱእ ታብ ኣሻ፥ የገሲ ዝኻነ ሩሕዞው ታብኣሸ። | 392. ደግ ሰው ሌላውን፥ መጥፎ ሰው ራሱን አስቸገረ። |
| 393. ከረቡ መሓጠሌ ደው ሐለ። | 393. ለከበሮ መቺ ፍየል ይሰጠዋል። |
| 394. ከረቡዚኘ ኢር ይፈርኩሜል። | 394. ከበሮአችን ፀሐይ አይችልም። (ወሬአችን በቀላሉ ይዳረሳል) ። |
| 395. ከረቢ ሲን ሲን ይኹንሜል። | 395. የከርቤ ጥርስ ጥርስ አይሆንም (የተውሶ ዕቃ እንደ ራስ አይሆንም) ። |
| 396. ከርሲ ረሐብ ይጠላል። | 396. ሆድ ራብ ይጠላል። |
| 397. ከርሲ ቂለቤ ኪሲወልዷ ሐልበ። | 397. በገራገር ሆድ ዲቃላ በቀለበት (ሬስዋን የልጠበቀች ዲቃላ ትወልድ) ገር መሆን ያስጠቃል። |
| 398. ከርሳምሌ ገበተ ሕደጉሎ ስናናምሌ ኡገ ሕደጉሎ። | 398. ለሆዳም ገበታ ለነገረኛ መንገድ ይተዋል። |
| 399. ከርስሌ ገለታም ኤለ። | 399. ለሆድ ውለታ የለውም። |
| 400. ከቢሬ ዮሉሜሉ ይሰቹሜሉ፥ አገኙ ጊር የሐግዱ ሜሉ። | 400. አስተማሪዎ እይበሉም አይጠጡም፥ ካገኙ ግን አይተውም። |
| 401. ከቢር ሚሽቲ ቱቃት፥ ቱቃት ባዬ ጊር ከታብ ሐጠብቲ። | 401. የመምህር ሚስት ታውቃለች ብትባል መጽሐፍ አጠበች። |
| 402. ከቢር ጋሬሌም አላኹ ኡሱእ ጋርሌን ባኹ ብላይ ባዩ። | 402. መምህር «ለቤቴ አላልኩም ለሌላ ቤት ነው እንጂ» አሉ። «መምህሩ ሠራተኛ ማታ ማታ ከጐረቤት እርሻ ማገዶ እየሰረቀ የማጣላቸው ኖሮ አንድ ቀን መምህሩ ሲሰብኩ «አትስረቁ» ሲሉ ሰምቶ ማገዶ ሳያመጣ ወደ ቤቱ መጣ። የመምህሩም ሚስት |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| | እራት ሳያዘጋጁ አመሹ። መምህሩ እራት ሲጠይቁ ይኸው ተነገራቸው። እሳቸውም ሠራተኛውን ጠርተው በቁጣ ቃል «ለቤቴ…» አሉ ይባላል። |
| 403. ከኒፉው ጪቅነዞሌ ኸደኖ | 403. የሠገራን ጉድጓድ ለግማቱ ቢከድኑት አክብረው የከደኑት መሰለው። |
| 404. ከዶ ጣእዜ ቡንዜ አሱ። | 404. የከዶ (ስም) ታዛዥነት ቡና በበርበሬ። |
| 405. ከፍትሳ ከፍ ዘየሰ ተሰትሳምተሰ ይላሜል። | 405. በሐዘን ጊዜ የማያዝን በደስታ ጊዜ አይደሰትም። |
| 406. ከፍትዋ ተስቲ ዘዩቅ ኡሱ እነሶ ቁቡሊንተ። | 406. ሐዘንና ደስታን የማያውቅ ሙሉ ሰብእና የለው። |
| 407. ኩሩምባዩው ሐማቺ ጌዩም አልፈረኬውም። | 407. ከርንን አማችም አይችለው። |
| 408. ኩሪ ሸረፈ ንጃት። | 408. ንብ ግድብ አፈረሰ (ነገር ሲጋነን) ። |
| 409. ኩሽ ሚሽቲ ትቡእ ቢኒ ከሕ። | 409. እጮኛ በሰማንያ ሚስት ትሆን። |
| 410. ኩዱው ኩፍቤ የናውጦ ሜል። | 410. ጉበት በሳንባ አይለውጡም። |
| 411. ኪልአሚር ይሎዛል ኪል ሐመድ ይልዛል። | 411. አልጋ ሲሉት አመድ። |
| 412. ኪዝ እቦችሌ ሔይዲዞንተ። | 412. ውሸት ለወንድ የወር አባባው (ነውሩ ነው) ። |
| 413. ኪዝ ዘሌመዱቦ አፍ ዱስ ዱስ ይላላ። | 413. ውሸት ያልተናገሩበት አፍ ማር ማር ይላል። |
| 414. ኮኦት እፊቀ ተካለሐ ኮኦት ዘር ተቃደሐ። | 414. ሁለት ቅል ተጠራራ፣ ሁለት ወንዝ ተቃዳ (ሰዎች መሰሎቻቸውን ሲረዱ የሚነገር ነው) ። |
| 415. ኮኦት ኢን እሳልቲ ሚን ቲቂሺ። | 415. ሁለት ዓይን እያለች ምንኛ ትናቅ (ዓይን እያለ አይመሰግንም) ። |
| 416. ኮኦት ኢጊር ሐሰኘሌ ኮኦት ለፉ ይሴቀሎሜል። | 416. ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ አይወጣም። |
| 417. ኮኦት ጋር ማይቤነ ይሊጥዛል ወልዲ ወልዲ ይኹኑ ሜል። | 417. በሁለት ቤት መሐል የሚያድግ ልጅ ልጅ አይሆንም። |
| 418. ኸያጥ ጋራ እራዝ ቲርትረ። | 418. የልብስ ሰፊ ልብስ ጠርዙ ትርትር (የውጭው እንጂ የራሱ ቤት አይሙዋላለትም) ። |
| 419. ኾኾኸ ዩጉሩሜል። | 419. መገዝገዝ አያርድም (ለማስፈራራት አልበገርም) ። |
| 420. ወሕሪ ሒልቅዞ ሳስአያም ጌይ ጉሩምትዞ ሺኢሽቲ እያም። | 420. የወር ቁጥሩ ሰላሳ ቀናት የከተማ ሰው ሐሜት ሶስት ዕለት። |
| 421. ወሕሪው ቀነኤ ጊር ጡይሌ አሰራም ኤሌ። | 421. ጨረቃ ከቀናት፥ ኮከብ ኃይል የላት። |
| 422. ወልዲ ብሉኡ አይሊ ብሪ ንቕሑ አይሊ። | 422. ህጻን ልጅ ብሎ አይል መቃብር ተነሱ አይል። |
| 423. ወልዲ ዲጂ ጊር ዋሊድ ቀረ። | 423. የልጅ ጉዳይ ከመጣ የወላጁ ይቀር። |
| 424. ወልዲኤ አለዋ ቀራም ኤለ። | 424. ለልጅ አገዳና ቀራ የለውም (እኩል ነው) (የማሽላ አገዳ ሲደርቅ ቀራ ይባላል) ። |
| 425. ወራብ ሐመድቤ ይበርዳል። | 425. ጅብ በአመድ ይበርዳል። |
| 426. ወራበሌ ወለመጥ ሐከመ ሞሽ። | 426. ለጅብ አንጀትን ልጓም አያደርጉም። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 427. ወራበ አሐድ ጊር ዘገኘቤው አታይቤ አሲር ጊር ይትግራገባል። | 427. ጅብ አንዴ በበላበት አስሬ ይመላለሳል። |
| 428. ወራበ ኢስሌጠ ቤሖርሴ ቡቺ ከልሐ። | 428. ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ። |
| 429. ወራበዋ ወጨረ አቱሸነ። | 429. ጅብና አህያ አታድርገን። |
| 430. ወራበ ዘዩቁበ ባድቤ ወሊ መሐመድን ተኝ ባየ። | 430. ጅብ በማይታወቅበት ሀገር ቅዱስ ነኝ አለ (ቆዳ አንጥፉልኝ አለ) ። |
| 431. ወራበ ዞለአቤው አታይቤ ይነትቃል። | 431. ጅብ በበላበት ገበታ ያስታውካል። |
| 432. ወር ዊሊአ ኡገ ሩሑቅ። | 432. ወሬው ገና መንገዱም ረጅም። |
| 433. ወር ይስጢም አልትቀበጠ መሐለቅ ይስጢ ብላይ። | 433. ገንዘብ የሚሰጥ እንጂ ወሬ የሚሰጥ አልታጣም። |
| 434. ወር ይቀርበኝቤ ኣዋ ጋር ምራስ የቅርበኝ። | 434. ወሬ ከሚቀርብኝ ከአባቴ የሚገኘው ውርስ ይቅርብኝ (ለወረኛ የሚተረት) ። |
| 435. ወስፊ ነቂ ወልዲም እስሌቅ። | 435. የስፌድ (ወስፌ) ሥራ ልጅ አላሳደገም (በቂ ገንዘብ አያስገኝም) ። |
| 436. ወቅቲ ዝገኜው ይሊፕዛል ዪድቃል። | 436. ጊዜ የጣለው በቁሙ ይወድቃል። |
| 437. ወናግ አገዱቤ ደው ደባል። | 437. በአንበሳ በረት የፍየል ጭፈራ። |
| 438. ወናግ አፍቤ ሳር ይቡኡ ሜል። | 438. በአንበሳ አፍ ሳር አይገባም። |
| 439. ወናግዞ ጊቢኛው አልፈረኬውም። | 439. አንበሳ እንኳ ሴራን አልቻለውም። |
| 440. ወንጠፍ ተሐይ ሑባብ። | 440. የምንጣፍ ሥር እባብ። |
| 441. ምንፊትቤ ሚይ ሜስብ። | 441. በወንፊት ላይ ውሃ መጨመር። |
| 442. ወደቀ ባዮ ጊር ተሰባበረ። | 442. ወደቀ ሲሉ ተሰባበረ። |
| 443. ወገር ዞለዴው አቁየ። | 443. ወይራ የወለደው ጉሉ (ያልዘሩት ሲበቅል) ። |
| 444. ወጨረሌ ዱስ ሚንዜ። | 444. ለአህያ ማር አይጥማት። |
| 445. ወጨረ ስብሐ ጊር ይትጐረ ኡሜል። | 445. አህያ ቢሰባ አይታረድም። |
| 446. ወጨረ ዝናም አሐድ ሚይ አልሰቸ። | 446. አህዮቻችን ከአንድ ወንዝ አልጠጡም (ምን አገናኘን) ። |
| 447. ወጨረዋ ሐመድዞ። | 447. አህያ ካመዱ። |
| 448. ወጨረ ጀነትዜ ሐመድ አይ። | 448. አህያ ገነትዋ አመድ ላይ። |
| 449. ወጨረዋ ወጨረ ሲን የሳብ ሩሜሉ። | 449. አህያ ለአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም። |
| 450. ወጨረ ኣን ኢስሞትኹ ቤሖርሴ ስርዱ አይብቀል ባቲ። | 450. አህያ እኔ ከሞትኩ ወዲያ ሣርዶ አይብቀል አለች። |
| 451. ወጨረ ፈስሌ ኡፍ ይለሕ ዶሜል። | 451. ለአህያ ፈስ አፍንጫ አይያዝም። |
| 452. ወጨረ ፈቲት ጭቆቲ ጊር ሩሕዜቤ አትሔጠርቲ። | 452. አህያ ገመድ በጠሰች ቢባል ማሰሪያዋን አሳጠረች። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 453. ዊጅ በሕ ዝዋለ ራጋው ሞተመ አገኞ። | 453. ከልጅ ጋር የዋለ ሽማግሌ ሙቶ አገኙት። |
| 454. ዊጅ ጠፍኹ ዩቁሜል። | 454. ልጅ ጠገብኩን አያውቅም። |
| 455. ዊጅዋ ራገ አጁቤ ይገባል። | 455. ልጅና ሽማግሌ በጊዜ ቤት ይገባል። |
| 456. ዊጅነት አልእቆት ደርመነት አልፍሮት። | 456. ልጅነት አላዋቂነት ወጣትነት ድፍረት። |
| 457. ዊጅዋ አተዋቅ አሳትቤ የቁምሳል። | 457. ልጅና ዶሮ በደጅ ያምሩአል። |
| 458. ዊጅ ዚሪኤው አዩሽነ። | 458. ልጅ ያየው አያድርገን (አይበረክትም) ። |
| 459. ዊጅዋ ፊቱው ይበርዳሜል። | 459. ልጅና ፊት አይበርደውም። |
| 460. ዊጅ ይሩጢተል ብላይ ይቀድሙሜል። | 460. ልጅ ይሮጣል እንጂ አይቀድምም። |
| 461. ዋሊ፤ ዘልኻነ ወሊ፤ ይኹኑ ሜል። | 461. በጊዜው ተጫዋች ያልነበረ ቅዱስ (ወሊዩ) አይሆንም። |
| 462. ዋይ ቢዝሐ ስሐቅ ዌር ቢዝሐ መሓከክ። | 462. የችግር ብዛት ሳቅ የእከክ ብዛት ማከኩ። |
| 463. ዘ ለመዳመው ተን ማገዴው። | 463. ያለመደን ጢስ አቃጠለው። |
| 464. ዘለሮኦ ቍሉእ። | 464. ያልተሟሸ ቅል። |
| 465. ዘለፎየ ጂን ጊርጊረ ዘለቀ መጠ ዱብ። | 465. ያላረፈ የጅን ጋቻ (ዕጣን ማጨሻ)፥ ያላረፈ ዱባ (ያላረፈ አደጋ ላይ ይወድቃል) ። |
| 466. ዘሌል ይፋጭዛል ዛልቤ ዩጫል። | 466. የሌለን (የሌላን) የሚፈልግ ያለውን ያጣል። |
| 467. ዘሌቆ ባረ አውዞው ገደለ። | 467. ያሳደጉት በሬ ባለቤቱን ገደለ። |
| 468. ዘሌቆ ቡዚዞ ይነኽሳል። | 468. ያሳደጉት ውሻ እንኳ ይናከሳል። |
| 469. ዘልሐረሬው ሐሪየ፥ ዛልግ ረገበ ወጨረ። | 469. የማይናደድ አሳማ የማይመለስ አህያ። |
| 470. ዘልሞተሌ አሐድ ያምሑሉፍ ይላተል። | 470. ያልሞተ ሰው አንድ ቀን ያልፍለታል። |
| 471. ዘልበልእኔውው ራት አየቴ ጨነ። | 471. ያልበላነውን ሥጋ ከጥርሳችን እናውጣ። |
| 472. ሀል በለአ አታዩው አይሓኮ። | 472. ያለመመን ቦታ አይኩም። |
| 473. ዘልሪኦ ሪኦ ናር ጊር፥ ዘል ስሞ ስሞ ናር ጊር ሱብሓን አለ ብላዩም አየሎዋ። | 473. ያላዩትን ካዩ፥ ያልሰሙትን ከሰሙ (አስደናቂ ነገር) የአላህን ስም እንጂ ሌላውን አያነሱ። |
| 474. ዘልሪአ መጋለ ይሮሌ ይደልላል፥ ዝቁሕ ዘልቃለቆዞን ይመስላል። | 474. ያላዩት ሀገር ያጓጓል፥ ወርቅ ይተለቀለቀ ይመስላል። |
| 475. ዘልሰጠ ቀሐት የውለድ። | 475. ንፉግ ሰውን ሴት ልጅ ይውስድ ይሷል። |
| 476. ዘልኻኔውቤ ዝነስእ ዝኻኔው ሰአ ፈተሐ። | 476. ለአቅመ አዳም ሳይደርስ ያገባ፥ ለዚህ ዕድሜ ሲደርስ ይፈታ። |
| 477. ዘልወለደ አልትዌረደ። | 477. ያልወለደ አልተገለገለ። |
| 478. ዘልወድቲ አይ አይ ቱኹኑ ሜት። | 478. ያልወለደች እናት እናት አትሆንም። |
| 479. ዘልወድትቤ ዋዩም ኤልቤ። | 479. ያልወለደች አልተቸገረች። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 480. ዘልገኘኔው ኡን አይፍለቀነ ዘልጩሐር ኔው እሳት አይማግድነ። | 480. ያልወረወርነው አይፈንከተን ያልጫርነው አያቃጥለን። |
| 481. ዘርቤ ኡን ግኙቦ፥ ዛልበ የውጠእባው። | 481. በወንዝ ድንጋይ ጣሉበት ያለውን እንዲያወጣ። |
| 482. ዘር ጀሚእ ደም ኻነ ጊር ደሚት ይመሎሖል። | 482. ወንዝ ሁሉ ደም ከሆነ ደም ይቀዷል። |
| 483. ዘር እመይ ሑሮ እየ ኮአ። | 483. ወንዝ ሳይወርዱ ውሃ አያፈሱ። |
| 484. ዘር እመይ ሑሮ እየ ኮአ። | 484. ወንዝ ሳይወርዱ ውሃ አያፈሱ። |
| 485. ዘርዋ ዘር የትቃዱሓል። | 485. ወንዝና ወንዝ ይቀዳዳል (ይረዳዳል) ። |
| 486. ዘሮው ሚንሌ ትክልሓኽ ባዮ ጊር ዛልበኝሌ ባየ። | 486. ወንዝ ሆይ ለምን ትጮሃለህ ቢሉት ስላለብኝ አለ። |
| 487. ዘየግኞ ቂስሚ ኢን ኑር የናቅሳል። | 487. የማያገኙትን ሲያዩ የዓይን ብሌን ይቀንስ። |
| 488. ዘዩቀኝ ወራበዮለኝቤ ዩቀኝ የብለእኝ። | 488. የማያውቀኝ ጅብ ከሚበላኝ የሚያውቀኝ (ጅብ) ይበላኝ። |
| 489. ዘይሕደሩቦ ጌይብ (አታይቤ) አየምኻሾ። | 489. አያድሩበት ከተማ (ቤት) አያምሻሹበት። |
| 490. ዘይትለመዱም ኤል ጀሐነም እሳት ብላይ። | 490. ያለገሓነም እሳት የማይለመድ የለም። |
| 491. ዘይትለዩም ኤል ዘይትራስ እዞ ኡሽነ። | 491. የማይለያይ የስም፥ የማይረሳሱ ያድርገን እንጂ። |
| 492. ዘይባር ይዘልሙሜል፥ ዘይይሙት ይትወለዴም። | 492. የማያባራ አይዘንብም፥ የማይሞት አይወለድም። |
| 493. ዘይሞቅ ዘይብረድ ኡን ቅባበ። | 493. የማይሞቅ የማይበርድ የድንጋይ ምጣድ። |
| 494. ዘይዛኝ ዝመስሌ ብቆጥ ገፍ አሻቲ። | 494. የማይነጋ መስሏት ቆጥ ላይ እዳሪ ወጣች። |
| 495. ዘገሕ ከርሲ ዛለ፥ ዘገሕ ባድቤ ወጠ። | 495. ሰፊ ሆድ ያለው፥ ከሰፊ ሐገር ይወጣ። |
| 496. ዘገኘሌ ቁይ፥ ዝቀበጠሌ ሕራር። | 496. ላገኘ ቁጣ፥ ላጣ ንዴት። |
| 497. ዘገኘዋ ዝሞተ ዝሕሊ ይቀብጡሜል። | 497. ያገኘና የሞተ ዘመድ አያጣም። |
| 498. ዘግ ዘላየ ዘርገሕ ባየ። | 498. በጅ ያላለ ዘርጋ አለ (ተሸፈነ) ። |
| 499. ዙንዙርትቤ ዘበለ ዩኩርመ ይሰጣል። | 499. በሰንዝር አልሰጥ ያለ ከንድቶ ይሰጥ። |
| 500. ዚምቢ ለእይቤ ዱስ ይክፍ ቶሜል። | 500. ዝምብ ባለበት ማይ አይከፈትም። |
| 501. ዚምጫ ጩቦ አታይቤ የደርቆ። | 501. ልብስን ባጠቡበት ቦታ ያደርቋል። |
| 502. ዚሞተ ሱምዞ ሓጂ። | 502. የሞተ ሰው ስሙ ሓጂ (ይከበራል) ። |
| 503. ዚሪኤው ወሕሪቤ ዘይሰም ኑሶ። | 503. ባየው ጨረቃ የማይጾሙበት (የማይታመን ሰው) ። |
| 504. ዚትሕራረሱቦ ጐጋው ጩቀመ ገኞ። | 504. በግብረ ሥጋ የተገናኙበትን ቆዳ ገምቶ ጣሉት። |
| 505. ዘትባለለ በለለ። | 505. የቸኮለ ተበላሸ። |
| 506. ዚትኮእ ሚይ ይትሐፈሱ ሜል። | 506. የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም። |
| 507. ዚትወለድኺሳዞን ሞትኺ። | 507. ከተወለድህ ሞትህ። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 508. ዚጥማሜ ዛገሩ ደበ ላይቤ ተኩላልቲ። | 508. ያጣጣመች ዝንጀሮ አውድማ ላይ ትንከባለላለች። |
| 509. ዛለ ሓጂ ዘሌለ ሮጂ። | 509. ያለው ሓጂ የሌለው ሌባ። |
| 510. ዛለ አይክለሕመ ዘሌለ አይቲጤነብ። | 510. ያለው ተጣርቶ የሌለው አያድምጥ። |
| 511. ዛለ ኩሙል፥ ዘሌለ ኩምቡሉል። | 511. ያለው ተመቻችቶ፥ የሌለው ተንከባሎ። |
| 512. ዛለ ዛለቤ ዩጫል፥ ዘሌለ ኢንዞ ዩጫል። | 512. ያለው ባለው፥ ይወጣ የሌለው ዓይኑ ይወጣ። |
| 513. ዛለ ደርቢ ጋር፥ ዘሌለ ሳር ጋር፥ ቅባጭዞ ክረ ጋር። | 513. ያለው ግንብ ቤት፥ የሌለው ሳር ቤት ይህንንም ያጣ ኪራይ ቤት። |
| 514. ዛለሌ ድበሉሎ። | 514. ላለው ጨምሩለት። |
| 515. ዛለሌ አሕሊ ሐለ። | 515. ያለው ዘመድ አለው። |
| 516. ዛሌ መሐለቅ፥ ዝሞተሌ ረሕመት። | 516. ላለ ገንዘብ፥ ለሞተ ርህራሄ። |
| 517. ዛል ሚሽል አሐድ ያምኢር ዩጭለሐል። | 517. ላለ ሰው አንድ ቀን ፀሐይ ይወጣለታል። |
| 518. ዛልባ ሐልበ ኡንቀቤ ኡን ሐልበ። | 518. ቆሎው ጠጠር አለው (ነገር አለው) ። |
| 519. ዛቄኝ ጥፊትቤ የምሐጠኝ። | 519. ስቸገር የረዳኝ በጥፊ ይምታኝ። |
| 520. ዛቆ ጅናምቤ ዘላቆ ይበዝሐል። | 520. ከታወቀ ዕብድ ያልታወቀ ይበዛል። |
| 521. ዛገሩ ፉዴዜ ሙሉጡው ትሩሜት። | 521. ዝንጀሮ የመቀመጫዋ መላጣ አይታያትም። |
| 522. ዚምቢ አልገደልቲ ግሩም ተትኒትቃት። | 522. ዝንብ ባትገድል ታስታውክ። |
| 523. ዜደ ቀበጠመ፥ ዜዶ አገኘ። | 523. የነገረ አጥቶ የተነገረው አገኘ። |
| 524. ዜገ ዩልደኝቤ ገደሊ የግደለኝ። | 524. ድሀ ከሚወልደኝ ሐብታም ይግደለኝ። |
| 525. ዜገ መዜገዞ ኢር ነቱ። | 525. የድሃ መንቀባረር የፀሐይ በሽታ። |
| 526. ዜገሌኝ ወራበ የቦርደኝ። | 526. የጀመረኝ ጅብ ይጨርሰኝ። |
| 527. ዜገዋ አንቀሩው ይክልሕ። | 527. ድሃንና ጨጓራን እየጮኸ ይበሷል። |
| 528. ዜገዋ ቅባጭ ወጨረዋ ሐመድ። | 528. ድሃና እጦት፥ አህያና አመድ (አይተጣጡም) ። |
| 529. ዜጐው ዘግ፥ ደረቅ ጐጐው ከከህ። | 529. ድሀ ይዘረጋ፥ ደረቅ ቆዳ ይጮህ። |
| 530. ዝረሐቤው ይጠፍዛል ይመስላሜል። | 530. የራበው የሚጠግብ አየምስለውም። |
| 531. ዝሮጅቲ ኢን ተቀድሚመ ትበካት። | 531. እይሰረቀች ዓይን አስቀድማ ታለቅሳለች። |
| 532. ዝ ሼመቆ ነቱሌ ደዋም ኤለ። | 532. ለደበቁት ህመም መድኃኒት የለውም። |
| 533. ዝቄሕ ቄሕ ዝቄሕ ይኹኑ ሜል። | 533. የሚያብረቀርቅ ሁሉ ወርቅ አይደለም። |
| 534. ዝቄሕ ዘልርእሌ ኔሕስ ዝቄ ሕዞንተ። | 534. ወርቅ ላላየ ነሐስ ወርቁ። |
| 535. ዝቆጮ ኢንጪቤ ዝቀረ ይበዝሓል። | 535. ከተቆረጠው እንጨት የቀረው ይበዛል። |
| 536. ዝበሰለ መታረ ዮለ ይቀብጡሜል። | 536. የበሰለ ሥጋ የሚበላው አያጣም። |
| 537. ዝበቀለ ወሕሪ አይቅበጠነ። | 537. የሚመጣ ወር አይጣን። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 538. ዝኻነ ኻነዋ እሩዚት አሩዝ አግቡኡኝ ባቲ። | 538. የሆነው ስለሆነ ሙሽሪት ልሞሽር አለች። |
| 539. ዝሽሹሎዋ ዝሽሹቦ። | 539. የፈለጉለትና የፈለጉበት (ሲያዳሉ) ። |
| 540. ዝዘለመቤው አታይቤ የባር። | 540. በዘነበበት ቦታ ያባራ። |
| 541. ዝዛቤው ወራበ። | 541. የነጋበት ጅብ። |
| 542. ዝገደረ አበ አውንተ፥ ዝገደርቲ አባይ አይንቴ። | 542. ታላቅ ወንድም አባት ታላቅ እህት እናት። |
| 543. ዝጠለእ አራትዞ ጠይንት። | 543. የጠሉት ምላሱ ጥቁር። |
| 544. ዝጠለእ ሓጀ ላምገፍቤ ዞደቀ ዝቄሒንት፥ ዞደዾ ሓጀ ፎለቤ ቱሉእ ኢንት። | 544. የጠሉት ነገር በእበት ላይ የወደቀ ወርቅ የወደዱት ነገር በሻኛ ውስጥ የገባ ትል። |
| 545. ዝጠልአ ሐማቺ ጌይቤ መጥረግ ሐፍ ያሽቦሐል። | 545. በጠሉት አማች ላይ መጥረጊያ ያነሷል (ለመጥረግ) ። |
| 546. ዝጠፊ አየሶረነ። | 546. የጠገበ አያስተናግደን። |
| 547. ዝጠፊ ወንደቅ ሕራትዞው ላቀን ኣሽ። | 547. የጠገበ አሽከር ራቱን ምሳ ያድርግ። |
| 548. ዝጠፊ ዝረሐቤውቤ ወሩም ኤለ። | 548. የጠገበ የተራበን አላወቀ። |
| 549. ዝጠፊ ጌይኡስእ ደርቢ የዳምስመ ይቺኻል። | 549. የጠገበ ሕንጻ አፍርሶ ይገነባል። |
| 550. ዝጠፉቦ ሲሪ ቆሽ ቆሽ ይላል። | 550. የጠገቡት ቂጣ ሊጥ ሊጥ ይላል። |
| 551. ዝጠፊ ይረሕባዛል ይመስላሜል። | 551. የጠገበ የሚርበው አይመስለውም። |
| 552. ዝጠፍቲ ወጨረ ቢሰሪተኩ ሳልቲ። | 552. የጠገበች አህያ ጋራ ላይ ትንደባለላለች። |
| 553. ዝፋሰሶ ሞት ሑንቀሖ አኮአ። | 553. ያሞገሱት ስፌድ ቆሎ አፈሰሰ። |
| 554. ዝሴቁቦቤ ይራግቦ (ሐል) ዝራጉቦቤ ይሙትቦ (ሐል) ። | 554. ባደጉበት ያረጁበት፥ ባረጁበት ይሞቱበት። |
| 555. ዝሽሽተ ኻንቲም ኣው ሚሽቲ ቲጢሙሜት። | 555. ምንም ደግ ብትሆን የእንጀራ እናት አትመሰገንም። |
| 556. ዝኸሮ ገዱቤ ዩቡኡቦ። | 556. በቆፈሩት ጉድጓድ ይገቧል። |
| 557. ዝሰጠ ዜገቤ ዚትቄበለ ይዘርፌ። | 557. ከሰጪ ድሀ ተቀባዩ ይባስ። |
| 558. ዝናረበውው ዝረሰአ ደም ጠረሽ። | 558. የነበረበትን የረሳ ደም አስታወከ። |
| 559. ዝናብ ዘለመ ጊር አውዞቤ | 559. ዝናብ ከዘነበ ባለቤቱ ላይ ያባራል። |
| 560. ዝዘሮው ይናጉ (ዩቁጮ) ። | 560. የዘሩትን ያጭዱ። |
| 561. ዝናብ ዝመሐጤው ወናግ አይዜገዱ መሰለ። | 561. ዝናብ የመታው አንበሳ ቀበሮ መሰለ። |
| 562. ዝጠሎ መሕማለልዞ ዞደዾ መቆመሶ። | 562. የጠሉት ማስቀየሙ የወደዱት ማማሩ። |
| 563. ዝዋይ ዋይ መታራው ጢሊ ጠለፍተ። | 563. በዋይታ የተገኘውን ሥጋ አሞራ ቀማችው። |
| 564. ዘሰአ አሞሰሰ ዝለበሰ አቆመሰ። | 564. የበላ ወዙ ታየ የለበሰ አማረ። |
| 565. ዞለእቲ ኢን የቃኼሒል። | 565. የበላች ዓይን ታፍራለች። |
| 566. ዘለዾ ኩሩእዞ ደወ። | 566. የወለዱት (ከንዱ) ትሹንም መድሐኒት። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 567. ዘሰዶዋ ዛረዶው የገኞ። | 567. የወለዱትንና ያስቀመጡትን ያገኟል። |
| 568. ዘደቀ ኢንጪቤ መንጨዋ ከልክ በዝሐቤው። | 568. የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል። |
| 569. ዘደዶ መሐዋው ቂመዞው ይሰብሮ። | 569. የወደዱትን ዕቃ ሊገዙ ሲዋዋሉ ዋጋውን ያሳንሷል። |
| 570. ዘደዶ ሱምዞ ኢድሪስ ዝጠሉ ሱምዞ ኢብሊስ። | 570. የወደዱትን ሰው ኢድሪስ የጠሉትን ሰው ሰይጣን (ይሏል) ። |
| 571. ዘደዶሌ ቀልቢ ቱልኩፍ ይላል ገማም ዘርገፍ ይላል። | 571. ለወደዱት ሰው ልብ ድነገጥ፥ ሹሩባም ዘርገፍ ይላል። |
| 572. ዘደድቲ ኢን ሩሕዜሌ ተሲናት። | 572. የወደደች ዓይን ራሷ ትናገራለች። |
| 573. ዘደዶ አፍዞ መዷ፥ ዝጠሎ አፍዞ ሲብሪ። | 573. የወደዱት አፉ መድ (ጥሩ ቀለም)፥ የጠሉት ግን ሬት። |
| 574. የምስሌ አዌ ሚስቲው ሙግረነትቤ ዘንገ ዘረአኹ ሌወ። | 574. የእንጀራ አናቴን ዕውነት ያምሰላት ወገሬ (የማሽላ ዓይነት) ብዬ ዘንጋዳ ዘራሁላት። |
| 575. የስጥመ የትፋልሲ። | 575. ሰጥቶ ያመስግን (አላህ) ። |
| 576. የሲኒዛል አራት፥ ይትረገፍዛል ሐጪ። | 576. የሚናገር ምላስ የሚገረፍ ጀርባ። |
| 577. የቲምሌ አሕሊም ኤለ። | 577. የሙት ልጅ የለው ዘመድ። |
| 578. የቲምዋ እሳት መንካከእ ይፈርኩሜል። | 578. የሙት ልጅና እሳት አይወድም መነካካት። |
| 579. የነታዛል ይሙትዛል ይመስለሐል። | 579. የታመመ የሚሞት ይመስለዋል። |
| 580. የእለፉቤ ዚትጌብቲ ኡፍይ ለፉብም ቲትጌበሌ ቁረቤ ሐልቲ። | 580. በዚህ ዛፍ ላይ ይረፈች ወፍ በዚህኛውም ላይ ልታርፍ ታቃርባለች። |
| 581. የገሲ ወልዷ አዋ አይ ሱም የትቂቅላል። | 581. መጥፎ ልጅ የወላጆቹን ስም ያጐድፋል (በመጥፎ ያስጠራል) ። |
| 582. የገሲ አመል እላ ቀብሪ አፍ ይትኼተላል። | 582. መጥፎ አመል እስከ መቃብር ይከተላል። |
| 583. የገድሮ ዘልሪአ የገድሩሜል። | 583. ሲያከብሩ ያላየ አያከብርም። |
| 584. የጠፍዛል ኡኻት ቅባበ ለአይቤ የታውቃል። | 584. የሚያጠግብ እንጀራ ምጣድ ላይ ያስታውቃል። |
| 585. የኸንለኸ ባየ ጊር ሳር ፈጥቤ ሐፍ ያሻል። | 585. ይሁንልህ ካለ በሳር ምሰሶ ያነሳል (አላህ) ። |
| 586. ዩሩጦዛል ዘገዶ ጪን ዩሩጦዛል ይትፈተሐል። | 586. ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል። |
| 587. ዩቅ አይትፈጅመ ዘዩቅ በሕአይሲረአነ (አይዳብለነ) ። | 587. የሚያውቅ ጠፍቶ ከማያውቅ ጋር አያገናኘን። |
| 588. ዩዳዛል ዘሌለ ይሒሞዛል ይመስላሜል። | 588. የሚወደው ሰው የሌለው የሚታማ አይመስለው። |
| 589. ዩጭ አባር ዘይውጠእሱም ሐደገ። | 589. የሚያልፍ ረሐብ የማያልፍ ስም እወረሰ። |
| 590. ያሪው ወልዷኸሹው ሚንኩትቤ ትሰሕሴሽ ባዬ ጊር ዘለድኼኩትቤ ባቲ። | 590. ጃርት ልጅሽን እንዴት አድርገሽ ትልሻታለሽ ቢሏት እንደ ወለድኳት አለች። |
| 591. ያሽ ዝቀቢጠ አምበዋ ጊሽጠ አትዋለደ። | 591. ሥራ የፈታ ማንጐንና ጊሽጣን አዳቀለ። |
| 592. ይሒከቤ ዩሕጢ ሐልበ። | 592. በሚያኝክ ዋጭ አዘዘበት። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 593. ይለብስዝቀበጠ ኡሱእ እራዝቤ ቀለጠ። | 593. ይለብሰው ያጣ በሰው ልብስ ኮራ። |
| 594. ይሊጦ ይሊጦመ ጋር ይጢሶ ይጢሶመ ዛላሑ ኤቀድ። | 594. ዞሮ ዞሮ ከቤት ኑሮ ኑሮ አላህ ፊት (ይመለሷል) ። |
| 595. ይሎ ስመእመ ጢሪ ኡን ወሐጠ | 595. ሲባል ሰምቶ ድንጋይ ዋጠ። |
| 596. ይበከለ ዝቀበጠ በሪ ጐይተሌ በከ። | 596. ያለቅለለት ያጣ ለከተማ በረኛ እለቀሰ (በሩቁ ለሚያውቀው |
| 597. ይበከባኩት ዘላቀ ረቀ ወራሺዞ ከርሲው እገረ። | 597. እንዴት እንደሚያስለቅስ ያላወቀ ሞኝ የአውራሾቹን ሆድ አራቀ (አስቀየመ) ። |
| 598. ይስጢ አየትቄብጢ። | 598. የሚሰጥ አያሳጣ። |
| 599. ይነኩሎ ጊር ዘላቀ ይነኮ ጊሩም ዩቁሜል። | 599. ሲነኩትለት የማያውቅ ስነኩትም አያውቅም። |
| 600. ይው አቀመ ሑባቡው ኢጊር ኸተሬው። | 600. እባብ የልቡን አይቶ እግር ነሳው። |
| 601. ይደልሒመ የዲልሒዛቤል ሰላመት ዩጨነ። | 601. ተሳስቶ ከሚያሳስት አድነን። |
| 602. ይጠሎዛል ይሒሞዛል ዩዶ ዛልዮሎዛል ይዲጃል። | 602. የሚጠሉት ሲያሙት የሚወዱት ሲበሉ ይደርሳል። |
| 603. ይፊረ ዘሌላው ኡሩስዞው ፍሮ። | 603. የሚፈራው የሌለው ራሱን ፍሩት። |
| 604. ዮለኘአቤ ይገበኝ ሊቂሔ። | 604. ወንድሜ ገንዘቤን ሲበላው ብድሬ እንደተመለሰልኝ (እቆጥረዋለሁ) ። - ሳህን ላይ እንደፈሰሰ ቅቤ። |
| 605. ዮሎዛል ዝላኸ። | 605. ሲበሉ የላኩት (ልቡ ምግቡ ላይ ስለ ሚሆን የተላከበትን ጉዳይ በሚገባ ሳይፈጽም ቀረ) ። |
| 606. ዮሊዛል ይረሕባዛል። | 606. ሲባላ የሚርበው። |
| 607. ሲባላ የሚርበው። | 607. ወተት የሌለው ሆጃና (ከቡና ቅጠል የሚፈላ እንደ ሻይ ያለ) ድሃ ባል መሳ ለመሳ። |
| 608. ደረቅ ቁጢ ሔጅጆ ሚን ይሪዝኒ ሐፍ አሾ ሚን ይኸፊ። | 608. ደረቅ ቁጢ (የቡና ቅጠል) ሲያዩት መክበሱ ሲያነሱት ግን መቅለሉ። |
| 609. ደረቅ የደርቃል። | 609. ደረቅ ያደርቃል። |
| 610. ደረቅ ጐጋው አሺሽ መቃበእ። | 610. ደረቅ ቆዳን ቅቤ መቀባት። |
| 611. ደረቅ ብሽ ከስ የቡርዳል። | 611. ደረቅ «ማስቲካ» ሞራ ይጨርሳል። |
| 612. ደሰ ሌቀ ጊር አይታዞቤ ዩድቃል። | 612. ኩይሳ ቢያድግ እቦታው ይወድቅ። |
| 613. ደባይ መትፌቀርዜ ብላይ መኽጀጀዜ የቁምሱሜል። | 613. ጥጃ መጫወቷ እንጂ መራገጧ አያምርም። |
| 614. ደቺ አሺር ዘቦረደመ ሰሚ አሺርሌ ይትማሐጥዛል። | 614. መሬት ያለውን ትምህርት ጨርሶ ሰማይ ላለው የሚያጥር (ሁሉን ነገር ያለኔ ማን ያውቃል የሚል) ። |
| 615. ደቺ ዩሸነ። | 615. መሬት (ቻይ) ያድርገን። |
| 616. ደቺቤ ዘልትካሐለ ለፉ መስይሴቀሉሜል። | 616. መሬት ሆኖ ያልተስማማ ዛፍ ላይ አብሮ አይወጣም። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 617. ዶቺቤ ዛሉው ሐፍ አሻኽቤ ፎይቤ ዛሉው ቀብ ሞሽ። | 617. መሬት ያለውን አነሳለሁ በማለት እጉያ ያለውን መጣል። |
| 618. ደወ ዘሌለ ነቱም ኤል። | 618. መድኃኒት የሌለው በሽታ የለም። |
| 619. ደው ኡልዳኸ ባቲመ ሩሕዜሌ አቦች ወለድቲ። | 619. ፍየል ልጅ እወልዳለሁ ብላ ባል የሚሆናትን ወስደች። |
| 620. ደው ኡስጡቤ ጋሚለ። | 620. ፍየል መሐል ግመል። |
| 621. ደው ኢንዜ ቁጢቤ። | 621. የፍየል ዓይን ቅጠል ላይ። |
| 622. ደዱው ዘገኘ ኪሕሊው አገኘ ኪሕሊው ዘገኘ ነብሪው እገኝ። | 622. ፍቅርን ያገኘ ስምምነትን ስምምነትን ያገኘ ድልን አገኘ። |
| 623. ዱሰ ዝጣንቲ ወጨረ ጥመዘው ቱቃሜት። | 623. ማር የተሸከመች አህያ ጣዕሙን አታውቀውም። |
| 624. ዱስ አትኹን ይለሕሱኸ መየቡርዱ ኻላ ሱጢም አትኹን ትመሪመ ትቀራኻ። | 624. ማር አትሁን እየላሱ ይጨርሱሃልና ኮሶም አትሁን መራራ ሆነህ እንዳትቀር። |
| 625. ዱስ ዛልበ አታይቤ ዱሰ ፈጅ ይትቀበጡሜል። | 625. ዱስ ዛልበ አታይቤ ዱሰ ፈጅ ይትቀበጡሜል። |
| 626. ዱባው ሐረግ ዘመዴው። | 626. ዱባን ሐረግ ሳበው። |
| 627. ዱፍ ዲጀ ጊር ምሻ ኢን። | 627. ንፋስ ሲመጣ ሁሉም ዓይኑን (ይይዛል) ። |
| 628. ዲነት ሐማቺ ጌይ ጢፊትቤ የትሚሕጣል። | 628. የራስ ገንዘብ በጥፊ ያስመታል። |
| 629. ዲነትሌ አው ብላይ እዜሩም ኤለ። | 629. ለሐብት አባት እንጂ አጐት የለውም። |
| 630. ዳይ መቀጡ ይበሰሉሜል። | 630. የጋራ ወጥ አይበስልም። |
| 631. የጋራ ወጥ አይበስልም። | 631. ሥራ መፍታት የቀበሩትን ያስወጣል። |
| 632. ድናዲን ሐጂ ኡሑራኸ ባትመ ሰገረቤ አገኜ። | 632. ኤሊ ሐጂ (መካ) እሄዳለሁ ብላ አሰገራ ተገኘች። |
| 633. ዶኸን ተሴሕቂ አሐድ ሲንዜ እልፊ ያጭዛል። | 633. ዝሆን ይሳቅ አንድ ጥርሱ ሺ የሚያወጣ። |
| 634. ጀዋ ጀነት እትማለሐ ጊር ጀነት አሰሌ ሐላወ ጀወከባቲ። | 634. ሥጋንና ጀነትን ቢያማርጧት ገንት የአላህ ነውና ሥጋ አለች። |
| 635. ጀዋብ ዝቄሕንተ ኢሰወጠ ቤሔርሌ ሜቲንቶ። | 635. ቃል ወርቅ ነው አንዴ ከተናገሩ ግን መዳብ ነው። |
| 636. ጂንዋ ጅናም አየግኘነ። | 636. እብድና ጂን አያግኘን። |
| 637. ጃይ ዱፍ ዘሌጤውው ገነዱፍ የርገብገሐል። | 637. የበጋ ነፋስ ይዞት የሄደውን የክረምት ነፋስ የመልሰዋል። |
| 638. ጃይቤ ዘይነዲ እሳቱም ኤል። | 638. ጃይቤ ዘይነዲ እሳቱም ኤል። |
| 639. ጅናምሌ ኡን መቁበል። | 639. ሰእብድ ድንጋይ ማቀበል። |
| 640. ገርጐረ ወልዲ ብሩቅዞ ይት ወለዳል። | 640. የነብር ልጅ ዥንጉርጉሩ ይወለዳል። |
| 641. ገበተቤ ዚትኮአ አሺሽ። | 641. በገበታ ውስጥ የፈሰሰ ቅቤ። |
| 642. ገፍ ለአይቤ ገማዶር። | 642. በዓይነ ምድር ላይ እያሉ ሹሩባ መሠራት። |
| 643. ገፍ ቢልሐ ደቺው እልነደላም። | 643. የዓይነ ምድር ሰለት አይበሳ መሬት። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 644. ገፍ ዲጀ ገዱ ኸሩ። | 644. ዓይነ ምድር መጣ ጉድጓድ ቆፍሩ (ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ) ። |
| 645. ጉመ ዘሌለ አይግደለነ። | 645. ካሣ የማይሰጥ አይግደለን። |
| 646. ጉር ዘላየ ዝናብ አይመሐጠነ። | 646. ነጐድጓድ የማይሰማ ዝናብ አይምታን። |
| 647. ጉነዋ መጐት አልከፈላም። | 647. ማባብያ ብድር አይከፍልም። |
| 648. ጉድ መሪ ጉድ ኺታተ። | 648. የመጀመሪያ ባል (ሚስት) ጉድ ደባቂ። |
| 649. ጉዶዞም ይገዻል። | 649. ጉቶም ይቸግራል። |
| 650. ጊሼሌ ዘላያው ወራብ በለኤው። | 650. ለነገ የማይልን ሰው ጅብ በላው። |
| 651. ጊዷር ስናን ሐለኝ ባይትቤ ጥቅሾ ድላገ ሐለይ ባይቲ ይማኛል። | 651. ትልቅ ነገር አለኝ ከማለት ትንሽ ሥራ አለኝ ማለት ይሻላል። |
| 652. ጋሚለ ሒሪረዞው ይሒጃል። | 652. ግመል ፊት ለፊት የሚሄደው መሪውን ያያል። |
| 653. ጋሚለ መርስስ ተፈጀ ጊር ወጨረሌ ዮቃል። | 653. የግመል ድብዳብ ሲያረጅ ለአህያ ይበቃል። |
| 654. ጋሚለ ሸሐትኩት ኪል ኤሔር አተትቁረነ። | 654. እንደ ግመል ሽንት ወደ ኋላ አታስቀረን። |
| 655. ጋሚላው ጤኖ ጊር ወጨረ ከልሐ። | 655. ግመል ለተጫነ አህያ ጮኸ። |
| 656. ጋሩው ጋምበሪዞቤት ዩቡኣሖል። | 656. ወደ ቤት በበሩ ይገባል። |
| 657. ጋር ሐለኝ ቢወርቃ ወቅሪ ሐለኝ ቢለፉ። | 657. ቤት አለኝ በወርቃ (የቦታ ስም) ቀፎ አለኝ በዛፍ ላይ። |
| 658. ጋሬይ ገራዴይ አፍዲጂይ አሚፊይ። | 658. ቤቴ የኔ ገራዳ (የአካባቢ ተጠሪ) ማድ ቤት የኔ ንጉሥ። |
| 659. ጋርሌ ቱመ እባትሌ ሹንኩርተ። | 659. ለቤቱ ነጭ ሽንኩርት ለውጭ ግን ቀይ ሽንኩርት (በቤት የሚያቃጥል ለውጭ ሰው ግን ወተት) ። |
| 660. ጋር ዝመሐጤውው ጋርበሪ ተቀበሌው። | 660. ቤት የመታውን በር ተቀበለው። |
| 661. ጋር አኮአ ጊር ጉንበ ይስቡቦሖል። | 661. ቤት ካፈሰሰ ጉንባ (አጥባቂ አፈር) ይጨምርዋል። |
| 662. ጋር ይጠርጐመ አባት ዩጮሖል። | 662. ቤት ጠርገው ደጅ ይወጡአል። |
| 663. ጋር ዞቤ ይትባለእዛል ቡቼተ። | 663. በቤቱ የሚባላ ውሻ ብቻ። |
| 664. ጌል ዘሌሌ ቢሰገረ ትበኪ። | 664. ጓደኛ የሌላት ሰገራ ውስጥ ታለቅስ (የምታማክረው ስለሌላት ብቻዋን ታወራለች) ። |
| 665. ጌይ ኡሱእ መሐሌ ረሐብ እሳልበ ጠፍኹ ይላል። | 665. የከተማ ሰው እየራበው በይሉኝታ ጠገብኩ ይላል። |
| 666. ጌይ ኡሱእ ዝደነቂውሌ ደቺ ቆንጡ ይላል። | 666. የከተማ ሰው ሲገረም እምሬት ቆንጡ ይላል። |
| 667. ግዳጅ ዛዩሻኩቱም ኤል። | 667. ግዳጅ እንደማያደርግ የለም። |
| 668. ጐ ጋው ሩጠዞ ይጋምሎሐል። | 668. ቆዳን በእርጥብነቱ ያጥፉእል። |
| 669. ጠበቀት ዱዋእ የለምዳል እዋ እይ ሙት ቢኪት የትሊምዳል። | 669. ችግር ምርቃት፥ የወላጅ ሞት ለቅሶ ያስተምራል። |

| ሐረሪ | አማርኛ |
|---|---|
| 670. ተይ ወልዷ ቀበጥኺለኝ ጊርቄሕ ወልዷን ቀበጥኺለኝ። | 670. ጥቁር ልጅ ብታጣልኝ ቀይ ልጅ አጣህልኝ? |
| 671. «ጠይ እማመትዋ ቄሕ አራት ዛላቤ ተቁረሕ» ባየ ሑባብ። | 671. እባብ «ጥቁር ከጠመጠመና ቀይ ምላስ ካለው ተጠንቀቅ» አለ (ከሰው ተጠንቀቅ ማለት ነው።) |
| 672. ጠፎ ጊር በስቹ ያሾሖል ረሐበ ጊር ሚን ኦሊ ይሎሖል። | 672. ሲጠግቡ ይደግሱ ሲርብ ግን ምን ልብላ ይሉ። |
| 673. ጡፈዋ ረሐብ ይትፈረኩሜሉ። | 673. ጥጋብና ረሐብ አይቻሉም። |
| 674. ጡፈ ጡፍጡፍ የትቢላል ረሐብ የትፋጃል። | 674. ጥጋብ ቂጣ ያስበላል ረሀብ ያፋጃል። |
| 675. ጢትቤ ዘልቂቤቀ በጇሑም ዮቃሜል። | 675. ትንሽ ያልበቃው ትልቅም አይበቃው። |
| 676. ጢት ይስጦመ ጣን ይፋጮሜል። | 676. ትንሽ ሰጥቶ ትልቅ አይፈልጉም። |
| 677. ጢት ዘለገደረ ጊዷሩም የገድሩሜል። | 677. ትንሽን ያላከበረ ትልቅንም አያከብርም። |
| 678. ጣን ሹምቡረ ቢቁምቁም ተፈጀ። | 678. ጭነት ሸንብራ በመቀንጠብ ያልቅ። |
| 679. ጣይ በስርዋ አሕሊ ሰናን የበርዶ ይኽሻል። | 679. የበግ ሥጋና የዘመድ ጥል ያበርዱት ያሻል። |
| 680. ጥለቤ ጠዋሮ ሐልበ። | 680. በየዋህነት ሳይፈልጉ ማርገዝ አለበት (ዲቃላ) ። |
| 681. ጥለቤ እለ ሐልበ። | 681. በየዋህነት መጐዳት አለ። |
| 682. ጦኛም ሚሽቲ አይንቴ | 682. ጥሩ ሚስት እናት ናት |
| 683. ፈራቱ አይዞ ተሐይቤ ዩጨ ሜል | 683. ፈሪ ከእናቱ ስር አይወጣም |
| 684. ፉዷው መምረጥመ ኡሩሱው መልበስ | 684. መቀመጫ ገልቦ እራስ ማልበስ። |
| 685. ፊገ ዛሻ ባረ ነፍሲዞው ገደለ። | 685. ደንብሮ የሸሸ በሬ ራሱን ገደለ |

## መኽማኸ

ይህ «መኸማኸ» የተባለው የሐረሪ (አደርኛ) ምሳሌና ተረት ከነአማርኛ ትርጉሙ ለማንኛውም አንባቢ እንዲያመች ተደርጎ በፊደል ቅደም ተከተል ቀርቦአል ። መጽሐፉ በሁለቱም ሕዝቦች መካከል ያለውን የባሕል ግንኙነት ለማጥናት ለሚሹ ምሁራን ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY